# ፀረ ሙስና

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS & ANTI-CORRUPTION COMMISSION
1993
ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

ፀረ-ሙስና ቅፅ 1 ቁጥር 1 ሐምሌ 2014 ዓ.ም በነፃ የሚታደል



# ሌብነት ላይ ጠንከር ያለ እርምጃ መወሰድ እንዳለበት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አህመድ አሳሰቡ

በሀገራችን ጌጥ፣ ልምምድና ነውር የማይታይበት እየሆነ በመጣው ሌብነት ላይ በቀጣይ ዓመት ጠንከር ያለ እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ደ/ር አብይ አህመድ አሳሰቡ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በ2014 የማክሮ ኢኮኖሚ አፈፃፀምና በ2015 በጀት ዓመት እቅድ ውይይት ላይ እንደተናገሩት በተለያዩ ዘርፎች ኢኮኖሚያዊ እድገት ብናስመዘግብም በየስራ ቦታችን በሌብነትን ላይ ጠንከር ያለ እርምጃ ካልወሰድን ዋጋ የለውም፡፡

በግብርናና በሌሎችም ዘርፎች ያመጣነው እምርታ ከፍተኛ ቢሆንም ለእያንዳንዱ አገልግሎት ገንዘብ እየጠየቅን ህዝብን የምናማርር ከሆንን በአንድ በኩል ያለማነውን በሌላ በኩል ማፍረስ ነው የሚሆነው፡፡ በመሆኑም እዚህ ጉዳይ ላይ በቀጣይ ዓመት ጠንካራ ስራ መስራት ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

ሌብነት ማንም ሰው ሳይሰጋ ገንዘብ የሚሰበስብበት ልምምድ መሆን የለበትም፡፡ ይህ ከሆነ ከፍተኛ ጥፋት የሚያስከትል ስለሆነ በዚህ ጉዳይ ላይ በ2015 በጀት ዓመት በትኩረት እንደሚሰራ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በአፅዕኖት ተናግረዋል፡፡



# “ፀረ-ሙስና” የተሰኘው የኮሚሽኑ ጋዜጣ በይፋ መጀመሩን የሚያበስር ፕሮግራም ተካሄደ



የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን “ፀረ-ሙስና” በሚል የተሰየመ በየወሩ የሚታተም ጋዜጣ ሥራ በይፋ መጀመሩን ለባለድርሻ አካላት ለማብሰር ፕሮግራም አኳሂዷል፡፡

ጋዜጣው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት፣ የፍትህ አካላት፣ የመገናኛ ብዙኃን የሥራ ሀላፊዎችና ባለሙያዎች፣ የክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ተቋማት እንዲሁም የሲቪክ ማህበራት በተገኙበት ሰኔ 24/ 2014 ዓ.ም በይፋ ተጀምሯል፡፡ በመድረኩ ላይ ለ”ፀረ-ሙስና” ጋዜጣ ግብዓት የሚሆኑ ጠቃሚ ሀሳቦች ከባለድርሻ አካላት የተሰባሰቡበት ነው፡፡

የፌደራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶ በጋዜጣው የማስጀመሪያ ፕሮግራም ላይ እንደተናገሩት ጋዜጣው የሚዲያ አማራጭን በማስፋት ረገድ ሚናው የላቀ ነው፡፡ መፈፀማቸው በተጨባጭ መረጃ ላይ የተመሰረቱ የሙስና ወንጀሎችንና በኮሚሽኑ የመከላከል ሥራ የተከናወኑና የሚከናወኑ ተግባራት ህብረተሰቡ እንዲያውቃቸው የሚደረግበት ጋዜጣ እንደሚሆን ገልጸዋል፡፡

“ፀረ-ሙስና”... ወደ ገፅ 2 የዞረ

# ሙስናን ለመከላከል ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያለው የወንጀል ምስክሮችና ጠቋሚዎች ጥበቃ ረቂቅ አዋጅ ላይ ምክክር ተካሄደ

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር ሙስናን ለመከላከል ከፍተኛ አስተዋፅኦ ባለው በወንጀል ምስክሮችና ጠቋሚዎች ጥበቃ ረቂቅ አዋጅ ላይ ሀገር አቀፍ የምክክር መድረክ አካሂዷል፡፡

የምክክር መድረኩ ዋና ዓላማ ረቂቅ አዋጁን ለማዳበር የሚያስችል ግብዓት ከባለድርሻ አካላት ማሰባሰብ ነው፡፡ አዋጁ በፌደራል መንግስት የሚወጣ ቢሆንም ሀገር አቀፍ ተፈፃሚነት ያለው

ሙስናን ለመከላከል.... ወደ ገፅ 2 የዞረ

# ኮሚሽኑ በብሄራዊ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ላይ ያካሄደው አስቸኳይ የሙስና መከላከል ጥናት ውጤታማ እንደነበር ተገለፀ



የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በሙስና ወንጀል ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር የዋሉት ኮሚሽነር ምትኩ ካሳ ይመሩት በነበረው የብሄራዊ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ላይ ያካሄደው አስቸኳይ የሙስና መከላከል ጥናት ውጤታማ እንደነበር ተገልፆል፡፡

በወቅቱ ጥናቱን ያስተባበሩት በኮሚሽኑ የሙስና መከላከል ቡድን መሪ የነበሩት አቶ ተስፋዬ በቀለ እንደገለፁት ኮሚሽኑ ከሁለት ዓመት በፊት በብሄራዊ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ላይ ያካሄደው አስቸኳይ የሙስና ጥናት አሁን በተቋሙ አመራር ላይ ለተወሰደው እርምጃ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡

በኮሚሽኑ የተካሄደው ጥናት የህግ አስፈፃሚ አካላትን ጨምሮ ለሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ተደራሽ ተደርጓል፡፡ እርምጃው የተወሰነ ጊዜ ይውሰድ እንጂ ውጤቱ ጥሩ እንደነበረ ተብራርቷል፡፡

ኮሚሽኑ ያጠናው ጥናት ዋነኛ ትኩረት ብሄራዊ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ኤልሻዳይ ሪሊፍ ኤንድ ደቨሎፕመንት አሶሴሽን ከተባለ መንግስትዊ ያልሆነ ገብረሰናይ ድርጅት ጋር በመመሳጠር በተረጂዎች ስም ለእርዳታ የተዘጋጀን ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሶች አላግባብ ለግል ጥቅም ውለዋል የሚል ነው፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ የብሄራዊ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ኮሚሽነር የነበሩት አቶ ምትኩ ካሳ በተረጂዎች ስም ለእርዳታ የተዘጋጀን ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሶች አላግባብ ለግል ጥቅማቸው አውለዋል በሚል ተጠርጥረው በቁጥጥር ሥር መዋላቸው ይታወሳል፡፡

# ኢትዮጵያ ታመስግን በሚለው ሀገራዊ ጥሪ መሠረት በኮሚሽኑ የምስጋና ፕሮግራም ተካሄደ

ኢትዮጵያ ታመስግን የሚለውን ሀገራዊ ጥሪ መሠረት በማድረግ የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን አመራርና ሠራተኞች "አንድ ሆነን እንስራ ኢትዮጲያ ታሸንፍ" በሚል መሪ ቃል ለሀገራችን ጀግኖች የምስጋና ፕሮግራም አካሂደዋል፡፡

በ18ኛው የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ያስመዘገቡትን ድል እና ሌሎች ጀግኖቻችን ለሀገራቸው ያበረከቱትን አስተዋፅኦ በማስመልከት በኮሚሽኑ የተካሄደው የምስጋና ፕሮግራም በደማቅ ሁኔታ ተከብሯል፡፡

በፕሮግራሙ ላይ ሁሉም የኮሚሽኑ አመራሮችና ሠራተኞች ቀኝ እጃቸውን ግራ ደረታቸው ላይ በማድረግ ለአንድ ደቂቃ በመቆም፣ ለአንድ ደቂቃ በማጨብጨብና የኢትዮጵያ የህዝብ መዝሙር በመዘመር እንዲሁም ፕሮግራሙን አስመልክቶ ሥነ-ግጥም በማቅረብ ጀግኖችን አመስግነዋል፤ ለኢትዮጵያ ያላቸውንም ክብር ገልፀዋል፡፡

በምስጋና ፕሮግራሙ ላይ የኮሚሽኑ ኮሚሽነር ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶ አትሌቶቻችን በጋራ በመስራት «ማሸነፍ እንዴት እንደሚቻል በተግባር አሳይተውናል ለዚህም ምስጋና ይገባቸዋል ብለዋል፡፡ አክለውም አትሌቶቻችን በዘር፣ በሀይማኖት፣ በአካባቢ ሳይከፋፈሉ በጋራ በመስራት ሀገራቸው በአለም መድረክ አሸናፊ እንድትሆን አድርገዋታል፡፡ ሀገርን ወደፊት ለማሻገር አንድነትን ከአትሌቶቻችን በመማር የሀገር ጠንቅ የሆነውን ሙስናን በጋራ በመከላከል ኢትዮጵያ እንድታሸንፍ እንሥራ ብለዋል፡፡

የኮሚሽኑ ም/ኮሚሽነር አቶ ወዶ አጦ በበኩላቸው አትሌቶቻችን ለእኛ በጋራ መስራትን አስተምረውናል፤ ሁላችንም በተገኘንበት የሥራ መስክ እንደ አትሌቶቻችን በጋራ በመስራት ሀገራችን ካለችበት የድህነት ቀንበር ማለቀቅ ይገባል ብለዋል፡ ፡ አትሌቶቻችን ብዙ ነገር አስተምረውናልና ምስጋና ይገባቸዋል ብለዋል፡፡





# የኮሚሽኑ አመራሮች የአረንጓዴ አሻራ መርሃ-ግብር አካሄዱ

አረንጓዴ አሻራ
GREEN LEGACY

የፌደራል የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን አመራሮች በምዕራብ አርሲ ዞንና ሻሸመኔ ከተማ ሐምሌ 9 ቀን 2014 ዓ.ም የአረንጓዴ አሻራ መርሀ-ግብር አካሄዱ፡፡

ለክቡር ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ተጠሪ የሆኑ ተቋማት ተሳታፊ የሆኑበት የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር የፌደራል የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽንም በዚህ መርሃ ግብር ላይ ተሳታፊ በመሆን የአረንጓዴ አሻራውን ማኖር ችሏል፡፡
ኮሚሽኑ ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ በአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ላይ ተሳታፊ የሆነ ሲሆን በዘንድሮው አመት ደግሞ ከአረንጓዴ አሻራ በተጓዳኝ አቅመ ደካሞችን የማገዝና የአካባቢውን ማህበረሰብ የልማት እንቅስቃሴ ቅኝት የማድረግ የክረምት በጎ አድራጎት ስራዎችን አከናውኗል፡፡

በኢትዮጵያ ባለፉት አራት ዓመታት 20 ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል ታቅዶ ከ23 ቢሊዮን በላይ ችግኞች መተከላቸውንና በቀጣይ ዓመትም ይህው ስራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል የማክሮ ኢኮኖሚ ኮሚቴ የ2014 በጀት ዓመት ሪፖርት ያመለክታል፡፡

# "ፀረ-ሙስና"...

ከገፅ 1 የቀጠለ

አክለውም በአሉባልታ ሳይሆን በትክክለኛ መረጃዎች ላይ በመመስረት የሚፈፀሙ የሙስናና ብልሹ አሰራር ግድፈቶችን በዚህ ጋዜጣ ላይ ይፋ በማድረግ ህብረተሰቡ በኮሚሽኑ የሙስና መከላከል ሥራ ላይ እምነት ኖሮት የፀረ-ሙስና ትግሉ አጋር እንዲሆን በማድረግ በኩል አይነተኛ የሚዲያ አማራጭ ይሆናል ብለዋል፡፡

የጋዜጣው መታተም በሙስና መከላከልና በፀረ-ሙስና ጉዳዮች ዙሪያ የጋራ ግንዛቤ እንዲኖር ከማስቻሉ በተጨማሪ የዜጎችን ነፃ አስተያየት ለማስተናገድ እድል እንደሚሰጥ በፕሮግራሙ ተሳታፊ የነበሩ ባለድርሻ አካላት ገልፀዋል፡፡

በኮሚሽኑ የሚዘጋጀው "ፀረ-ሙስና" ጋዜጣ በ2015 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ጀምሮ በየወሩ ለህትመት የሚበቃ ነው፡፡ በመሆኑም አስተማሪ በሆኑ የሥነምግባር፣ የሙስናና ብልሹ አሰራር ጉዳዮች ዙሪያ ለሚጽፉ አካላት በሩ ክፍት መሆኑንም ኮሚሽኑ ያሳውቃል፡፡

# ሙስናን ለመከላከል....

ከገፅ 1 የቀጠለ

በመሆኑ የሌሎች አካላትን ተሳትፎ በእጅጉ ይጠይቃል፡፡

በአዋጁ ላይ ድርሻ ከተሰጣቸው አካላት መካከል አንዱ የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ነው፡፡ ኮሚሽኑ በረቂቅ አዋጁ ዝግጅት ላይ ተሳታፊ እንደነበር የኮሚሽኑ የህግና አሰራር ጉዳዮች መምሪያ ሃላፊ አቶ ገዛኸኝ ጋሻው ገልፀዋል፡፡ እንደ አቶ ገዛኸኝ ገለፃ ረቂቅ አዋጁ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የሚያስችሉ ሀሳቦች የተካተቱበት ሲሆን ሙስናን ለመከላከልም ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡

በሥራ ላይ ያለው አዋጅ ቁጥር 699/2003 ያሉበትን ክፍተቶች እና በተግባር እያጋጠሙ ያሉ ተግዳሮቶችን የሚያሳይ ጥናታዊ ጽሁፍም ለመድረኩ ቀርቦ ውይይት የተደረገበት መሆኑን የኢፌዲሪ ፍትህ ሚኒስቴር አስታውቋል፡፡

## ርዕሰ-አንቀፅ

# የ2014 በጀት ዓመት ዋና ዋና ክንውን

የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ የብልጽግና ጉዞ ስኬትማ ለማድረግ በአገርዓቀፍ ደረጃ ሙስና እና ብልሹ አሠራርን መከላከል አንገብጋቢ ጉዳይ መሆኑ ታምኖበት ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ ይገኛል፡፡ ባለፉት የለውጥ ዓመታት በየደረጃው በሚገኙ የመንግሥት ተቋማት ውስጥ የአሠራር ሥርዓት ለማሻሻልና ግልጽነትና ተጠያቂነትን ለማስፈን የተደረገው ጥረት ተጨባጭ ውጤቶችን እያስገኘ ነው፡፡ ለዚህም ማሳያ የሚሆነዉ በብልሹ አሠራር ችግሮች ተደናቅፈው የነበሩና በብርቱ የሪፎርም እርምጃዎች ወደ ተግባርና አገልግሎት መስጠት የተሻገሩ አገራዊ የልማት ፕሮጀክቶችን ማስታወስ ይቻላል፡፡

የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከሌሎች ባለድርሻ አካላትና ህዝብ ጋር በመቀናጀት ሙስና እና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ተልዕኮውን ለመወጣት የአሰራር ሥርዓቱንና አደረጃጀቱን በመፈተሽ ጉድለቶችን ለይቶ ወደ ለውጥ እርምጃ ገብቷል፡፡ የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽንን ስልጣንና ተግባር እንደገና ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 1236/2013 ለዚህ ዋነኛ ማረጋገጫ ነው፡፡

አዋጁ የትውልድ የሥነምግባር እና የሞራል እሴቶችን በብቃት ለመገንባት፣ የሙስና ወንጀልንና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል፣ ለፀረ-ሙስና ትግሉ አጋዥ የሆነ የህዝብ ንቅናቄ በመፍጠር ህብረተሰቡ የፀረ-ሙስና ትግሉ ባለቤት እንዲሆን ከፍተኛ እገዛ የሚያደርግ ነው፡፡ ኮሚሽኑ በአዋጅ የተሰጠውን ይህን ተልዕኮ በአግባቡ መወጣት እንዲያስችለው የክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች ኮሚሽኖችን ያካተተ አገርዓቀፍ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች የትስስር ጉባኤ በ2014 በጀት ዓመት እንዲመሠረት በማድረግ ትግሉ በሀገርዓቀፍ ደረጃ በቅንጅትና በትብብር እንዲከናወን እየሠራ ይገኛል፡፡

የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በ2014 በጀት ዓመት ያከናወናቸው አገራዊ የሙስና መከላከል እርምጃዎች በሶስት የትኩረት አቅጣጫዎች ላይ የተመሰረቱ ነበሩ፡፡ በዚህ መሠረት ኮሚሽኑ አገራዊ የፀረ-ሙስና ትግል በሚገባ እንዲያስተባብር የራሱን ተቋማዊ አቅምና ብቃት የማሻሻል፤ የዜጎችን የሥነምግባርና የሞራል እሴቶችን የመገንባት እንዲሁም የሙስና መከላከል አገልግሎት የመስጠት ተግባራትን አከናውኗል፡፡

ተቋማዊ አቅምን ከመገንባት አኳያ በ2014 በጀት ዓመት የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ረቂቅ ፖሊሲና ስትራቴጂ ያዘጋጀ ሲሆን በቀጣይ በጀት ዓመት ተጨማሪ ውይይቶችን በማካሄድ አጠናቆ ተግባራዊ እንደሚያደርግ ይጠበቃል፡፡ የሙስና መከላከል ተግባርን ማስተባበር የሚያስችል መዋቅራዊ አደረጃጀቶችን የመከለስና የማሻሻል፣ የሙስናና ብልሹ አሠራር ወንጀል ምርመራና ክስ ተግባር በፍትህ ተቋማት እንዲከናወን የመረጃ ትስስርና ቅንጅት የመፍጠርና ውሳኔ ያገኙ የሙስና ወንጀሎችን መረጃ በማደራጀት ጥቅም ላይ እንዲውል የማድረግ ተግባር ተከናውኗል፡፡ የተቋማት አመራሮችና አግባብነት ያላቸው ሰራተኞችን ሀብት የመመዝገብና ትክክለኛነቱ እንዲረጋገጥ ለማድረግ የሚያስችል የዲጂታል ሥርዓት የመዘርጋት ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ በሌላ በኩል አገራዊ የሙስና መረጃ ማዕከል የማደራጀትና ከተለያዩ ምንጮች የሚቀርቡ መረጃዎችን የመለየት፤ የመተንተን፣ ለውሳኔ የሚሆን ምክረ-ሀሳብ የማመንጨት ተግባራትም ተከናውኗል፡፡ የሥነምግባር ግንባታና የሙስና መከላከል አቅም ግንባታ ሥልጠና ለፌዴራልና ለክልል ኮሚሽኖች አመራሮችና ባለሙያዎች ለማዘጋጀት ከዓለም አቀፉ የፀረ-ሙስና አካዳሚ ጋር የትብብር ማዕቀፍ የማዘጋጀት ተግባር ተከናውኗል፡፡

ኮሚሽኑ በዓመት እስከ ሃያ ሚሊዮን ብር ለቢሮ ኪራይ የሚያወጣውን ወጪ በማስቀረት የራሱን አሮጌ ህንፃ በማሳደስና ለሙስና መከላከል ተልዕኮ አጋዥ እንዲሆን የማዘመን ተግባር አከናውኗል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የፌዴራል መንግሥት የአስፈጻሚ አካላት የሥነምግባርና የጥቅም ግጭት መከላከያ ረቂቅ ደንብ የማዘጋጀት፣ የፌዴራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የራሱ ልሳን የሆነ "የፀረ-ሙስና ጋዜጣ" የማቋቋም፣ የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች የየራሳቸውን ኮሚሽን እንዲያደራጁና በከተሞች አከባቢ እየተባባሰ የመጣውን የሙስናና ብልሹ አሠራር ችግሮችን በጠንካራ አደረጃጀት ላይ ተመስርቶ ለመከላከል አስቻይ ሁኔታ ለመፍጠር ጥረት ተደርጓል፡፡

የሥነምግባር እና የሞራል እሴት ግንባታን በተመለከተ ኮሚሽኑ በ2014 በጀት ዓመት ከክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ተቋማት ጋር በመተባበር ለሙስና ተጋላጭ ለሆኑ የመንግሥት፣ የልማትና ህዝባዊ ተቋማት ሀላፊዎችና ሠራተኞች እንዲሁም ለሥነምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊዎችና ሠራተኞች በሥነምግባርና በሞራል እሴቶች ላይ የሥልጠና እና ግንዛቤ ማጎልበቻ ተግባራትን ማከናወን ተችሏል፡፡ በዚህ መሠረት በፌዴራል ተቋማት ለሚሰሩ 5000 አመራሮች እና ሰራተኞች በተመረጡ የሥነምግባርና የሙስና መከላከል ርዕሰ-ጉዳዮች ላይ ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ ከዓለም አቀፍ የፀረ-ሙስና አካዳሚ ጋር በመተባበር ለ50 የፌዴራል እና የክልል ኮሚሽኖች አመራሮች እና ሰራተኞች በሙስና ስጋት ጥናት፣ በጥቅም ግጭት እና አመራር ሥነምግባር ላይ የዓቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ ከዚህ ባሻገር በክልሎች የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች አማካኝነት በዞንና ወረዳዎች ለሚገኙ 1 ሚሊዮን 333 ሺህ 629 ለሚሆኑ የመንግስት ሰራተኞች፣ አመራሮች እና ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በሥነምግባር፣ በሞራል እሴቶች ግንባታና በሙስና መከላከል የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የአቅም ግንባታ ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

የሙስና ሥጋት ጥናት በማካሄድ የሙስና መከላከል አገልግሎትን የላቀ ማድረግ ሌላው በበጀት ዓመቱ የተከናወነ ተግባር ነው፡፡ ኮሚሽኑ በ2014 በጀት ዓመት የፌዴራልና የክልል የፀረ-ሙስና ተቋማት ለሙስና እና ብልሹ አሠራር ክፍተት ሊፈጥሩ የሚችሉ 62 አሠራሮችን እንዲሁም የፌዴራል ተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች ደግሞ 248 አሠራሮችን በድምሩ 310 ክፍተቶችን

በመለየት የሙስና መከላከል የአሰራር ሥርዓት ጥናት በማካሄድ የማሻሻያ ሀሳቦች ተግባራዊ እንዲሆኑ ለሚመለከታቸዉ ተቋማት ድጋፍና ክትትል ማድረግ ተችሏል፡፡ ጥናቶቹ የመንግስት ፕሮጀክትና ግዥ አፈፃፀም፣ የፋይናንስ አስተዳደር፣ የአገልግሎት አሰጣጥ እና በተለያዩ የአገልግሎት ዘርፎች የፈቃድ

አሰጣጥ ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡

የመንግስት ሀብት ለመመዝበርና ለማጭበርበር በሃሳብ ደረጃ የተጠነሰሱ ወይም በአሠራር ደረጃ የተዘጋጁ የጥፋት ሁኔታዎችን ወደ ሙስና ወንጀል ድርጊት ከመለወጣቸው በፊት ክልከላ እንዲካሄድ ከህብረተሰቡ የቀረቡ 2 ሺህ 348 ጥቆማዎችን በአስቸኳይ ሙስና መከላከል አገልግሎት እንዲቋረጥ በማድረግ በድምሩ 406 ሚሊዮን 128 ሺህ 318 ብር ከ 51 ሳንቲም የሚገመት ሀብትና ንብረት ማዳን ተችሏል፡፡ ከዚህም ሌላ 68 ሺህ 248.99 ካ/ሜትር የከተማ ቦታ እና 97.652 ሄክታር የገጠር መሬት እና ሌሎች በርካታ ዋጋ ያልወጠላቸው ንብረቶች ከምዝበራና ብክነት እንዲድኑ ማድረግ ተችሏል፡፡ በጥሬ ገንዘብም 275 ሚሊዮን 987 ሺህ 183.20 ወደ መንግስት ካዝና ተመላሽ ተደርጓል፡፡

ዘርፍ-ተኮርና መዋቅራዊ የሙስና ሥጋቶችን ለይቶ መከላከል አስፈላጊ አቅጣጫ መሆኑን በመገምገም በ2014 በጀት ዓመት በኢኮኖሚ ዘርፍ በገቢዎችና ጉምሩክ፣ በማህበራዊ ዘርፍ በትምህርት እና በአስተዳደር ዘርፍ ደግሞ ፍርድ ቤቶችን ከፌዴራል እስከ ክልል በተዘረጉ መዋቅሮች የሙስና ሥጋት ጥናት በማካሄድና ሪፖርት በማዘጋጀት የመጀመሪያ ዙር የባለድርሻ አካላት ውይይት ማድረግ ተችሏል፡፡

ከተለያዩ ምንጮች ከተገኙት 3 ሺህ 655 የሙስና እና ብልሹ አሠራር ጥቆማዎች መካከል የፌዴራሉና የክልል የፍትህ ተቋማት ውሳኔ የሰጡባቸው እና ለኮሚሽኖች የተላኩ የሙስና ወንጀል ውሳኔዎች መረጃ እንዳመለከተው የምርመራና ክስ ሥራዎችን በማከናወንና በማስቀጣት የተመዘበረ በጥሬ ገንዘብ 598 ሚሊዮን 804 ሺህ 254.44፣ 4,295 ካ/ሜትር የከተማ ቦታ እና ዋጋ ያልወጣላቸው በርካታ ንብረቶች ወደ መንግስት ካዝና ተመላሽ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ በዚህ ዙሪያ ጥቆማ የሰጡ 59 ጠቋሚዎችም ጥቃት እንዳይርስባቸው የህግ ከላለ ተሰጥቷቸዋል፡፡

ባለፉት አሥር ዓመታት ተጀምሮ ሳይጠናቀቅ የቆየዉን የዲጂታል የሀብት ምዝገባ አሠራር ሥርዓት በ2014 በጀት ዓመት በማጠናቀቅ ሥራ ላይ ማዋል ተችሏል፡፡ በዚህም ሀብት አስመዝጋቢዎች በአጭር ጊዜ ባሉበት ቦታ ሆነው ያለ ምንም እንግልት እና የመረጃ ንክኪ፤ ሀብታቸውን በዲጂታል ሀብት ምዝገባ ቅጽ እንዲያከናወኑ ማድረግ ተችሏል፡፡

በዲጂታል የሀብት ምዝገባ ስርዓት 6,537 የተቋማት የበላይ አመራሮችና ሌሎች የሥራ ሀላፊዎች የሀብት ምዝገባ እንዲያካሂዱ ተደርጓል፡፡ የተመዘገበ ሀብት መረጃ ትክክለኛነት ከማረጋገጥ አኳያም የ1,058 ሀብት አስመዝጋቢዎች መረጃ የተረጋገጠ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 382 ግለሰቦች ያስመዘገቡት መረጃ ትክክል ሆኖ ስላልተገኘ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ተደርጓል፡፡

ኮሚሽኑ በልዩ ሁኔታ የሙስና እና ብልሹ አሠራር ሥጋት ክትትል ከሚያደርግባቸዉ ተግባራት ውስጥ በዓለም ባንክ ድጋፍ የሚካሄዱ ፕሮጀክቶች ይገኙበታል፡፡ በዓለም ባንክ የበጀት ድጋፍ በሰባት ተቋማት ውስጥ ተፈፃሚ የተደረጉ ፕሮጀክቶች ከሙስና እና ብልሹ አሠራር በጸዳ ሁኔታ እየተከናወኑ ስለመሆናቸው የፕሮጀክት ተጠቃሚ ማህበረሰብ አካላትን በማሳተፍ የማረጋገጥ ሥራ በማከናወን ምክረ-ሀሳብና ሪፖርት ለዓለም ባንክና ለሚመለከተቸው ባለድርሻ አካላት ማቅረብ ተችሏል፡፡

ኮሚሽኑ በቀጣይም የተጀመሩትን ተቋማዊ ማሻሻያዎች በስፋት በማከናወን እና ከክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች፣ ከከተማ አስተዳደሮችና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን ትስስር በማጠናከር ሀገራዊ የሙስና መከላከል ሥራዎችን በብቃት ለማከናወን ጥረት ያደርጋል፡፡ ከመቼውም ጊዜ በላይ የፀረ-ሙስና ትግሉ ሕዝባዊ መሰረት እንዲኖረዉና የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ የላቀ እንዲሆን ለማድረግ በትኩረት ይሰራል፡፡

**ፀረ-ሙስና፤ በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ**

**አድራሻ**

**ስልክ** 011552-77-79
**ፖ.ሳ.ቁ** 34799
**ኢ-ሜይል** FeaccEthiopia2013@et
**ድረ-ገጽ** www.feacc.gov.et
**ፌስቡክ** www.facebook.com/feaccOfficial
**ቴሌግራም** t.me/feacc
**ትዊተር** www.twitter.com/EthiopiaFeacc
**ዩቲዩብ** Federal Ethics & Anti-Corruption Commission
**ለሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ስራዎች** www.feaccdars.gov.et

**ለፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና ወንጀል ጥቆማ መስጫ አድራሻዎች**

**ስልክ** 011552-77-92/ 011553-38-52
**ሞባይል** 0935947533
**ፖ.ሳ.ቁ** 34799
**ድረ-ገጽ** www.feacc.gov.et
**ኢ-ሜይል** CorruptionReportEthiopia@feacc.gov.et
**ቴሌግራም** t.me/CorruptionPointing
**ዋትስአፕ** wa.me/qr/5IGXTSIYUMPBF1

# ቆይታ

## “ባሉብን የሥነምግባር ህመሞች ላይ ሙስና ሲጨመር ለማገገም በእጅጉ ይከብደናል!”

ዶክተር ጠና ደዎ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የፍልስፍና ትምህርት ክፍል መምህር

የ”ፀረ-ሙስና” ጋዜጣ ቅፅ አንድ የመጀመሪያ ዕትም እንግዳችን በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በፍልስፍና ትምህርት ክፍል ለበርካታ ዓመታት በመምህርነት በማገልገል ላይ ያሉ ዶክተር ጠና ደዎ ናቸው፡፡ ዶ/ር ጠና በሥነምግባር እና በግብረገብ መስክ በርካታ ጥናቶችን አድርገዋል፤ ፅሁፎችንም በጋዜጦች እና በመፅሔቶች ላይ በመጻፍ ለአንባቢያን እንዲደርስ አድርገዋል፡፡ “ሰው ግብረገብ እና ሥነምግባር: የዘመናችን ቁልፍ ጉዳዮች” በሚል ርዕስ በ2008 ዓ.ም ያሳተሙት ዳጎስ ያለ መጽሐፍ ከዶ/ር ጠና ሥራዎች መካከል ተጠቃሽ ነው፡፡ በሥነምግባርና በግብረገብ ዙሪያ የቻሉትን ሁሉ ለመሥራት ከፍተኛ ፍላጎት እንዳላቸው የሚናገሩት እኚህ ምሁር ወደዚህ ዘርፍ ያዘነበሉበት ዋና ምክንያት የሥነምግባር ችግር በዚህ ዘመን ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ የሰው ልጆች ቁልፍ ተግዳሮት መሆኑን በመረዳታቸው እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ የሥነ-ምግባር ችግር ዛሬ በሁሉም ቦታ ይታያል፣ በማህበረሰብ ውስጥ በህዝብና በመንግስት መካከል ይህ ችግር በጉልህ ይስተዋላል፡፡ በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እንዲሁም በባህላዊ ጉዳዮች ዙሪያ ከሚስተዋሉ ችግሮች መካከል ከሥነ-ምግባር ጋር የሚያያዙት ላቅ ያለ ድርሻ ይኖራቸዋል የሚሉት ዶ/ር ጠና ሰው በግብረገብ እና በሥነምግባር ውስጥ ያሉ መርሆዎችን በትክክል ተግባራዊ በማድረግ ዓለምን ከከፋ ችግር በቀላሉ ማላቀቅ ይችላል የሚል እምነት አላቸው፡፡ የ“ፀረ-ሙስና” ጋዜጣ በሥነምግባር” ርዕሰ ጉዳይ ላይ ከዶ/ር ጠና ደዎ ጋር ያደረገችውን ቆይታ ይዞ ቀርባለች፡፡ መልካም ንባብ!



ፀረ-ሙስና፡- ሥነምግባር ማለት ምን እንደሆነ ቢያብራሩልን፤ ግብረገብ የሚለው ጽንሰ ሃሳብስ ምንን ያመለክታል?

ዶ/ር ጠና ደዎ፡- እነዚህ ሃሳቦች ብዙ ጊዜ እየተደበላለቁ ያስቸግራሉ፡፡ ሥነምግባር በርካታ ብያኔዎች አሉት፡፡ የሰውን ባህርይ የምንገልጽበት፣ ድርጊቱን የምንመረምርበት፣ የምንፈርጅበት እና የምንበይንበት ነው፡፡ በዚህም ሳቢያ እንደ ድርጊት ወይም ባህርይ መመሪያ (መስፈሪያ) ተደርጎ ይታሰባል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የግብረገብ ፍልስፍና (moral philosophy) ነው፡፡ በጥናት መስክነቱ ግብረገብን ያጠናል፡፡ ስለዚህ ሥነምግባርን በአንድ በኩል የሰው ድርጊትና ባህርይ መመሪያ በሌላ በኩል ግብረገብን የጥናት መስክ አድርጎ የሚንቀሳቀስ ሰፊ የፍልስፍና ቅርንጫፍ ነው፡፡

ግብረገብ ደግሞ መልካም እሴቶችን የምናሳድግበትና እኩይ ባሕርያትንና ተግባራትን የምናስወግድበት የአስተሳሰብ ዘርፍ ነው፡፡ እንደሚታወቀው የሰው ልጆች በአጠቃላይ መልካም ነገር ማሰብና መስራት ያስደስታቸዋል፤ ሁሌም በጎ ሰው መሆንና በጎ ነገር ማድረግ ምርጫቸው ነው፡፡ ሰናይ ምግባራትና ተግባራት ለሰዎች ጥያቄ መልስ ለመስጠት፣ ችግሮችን በተሻለ መንገድ ለመፍታት ብርቱ ጉልበት አላቸው፡፡ በተቃራኒው ሰዎች በመርህ ደረጃ እኩይ አስተሳሰቦችንና ተግባራትን ይጠላሉ፤ መጥፎ ሥራዎችን ማስወገድ ምርጫቸው ነው:: በዚሁ መሠረት የተፈጠረ ግብረገብ ጥሩነትን ስለማዳደግ እና መጥፎነት ስለማስወገድ የሚያወሳና የሚያስተምር የሰው ልጆች የአስተሳሰብ ዘይቤ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ከህይወታችን ጋር ቀጥተኛ ቁርኝት አለው፡፡

ህይወትን ያለጥርጥር እንወዳታለን፡፡ ይህ እውነት ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ህይወትን የሚጠቅምና የሚያከብር፣ የሚንከባከብና የሚያመቻች ተግባራትን ማከናወን ሁሌም ተመራጭ ይሆናል፡፡ እነዚህ ተግባራት በግብረገብ ይገለጻሉ፡፡ ሰብአዊ ፍጡር የሆነው ሰው ያለግብረገብ የኖረበትና የሚኖርበት ጊዜ የለም፡፡ የሰው ማንነት ያለ ግብረገብ ከታሰበ ሰብአዊ ፍጡር መሆኑ ቀርቶ አውሬ ይሆናል- የሚጠቅምና የሚጎዳ፤ መልካምና መጥፎ፤ ትክክልና ስሕተት ድርጊትና ባህርይ ለይቶ የማይረዳ እንስሳ ይሆናል፡፡ ግብረገብ የሰው ልጆች ግኝት ነው፡፡ ከማንኛውም የዕውቀትና የክህሎት ዘርፍ ለሰው እጅግ ቅርብ ነው - ግብረገብ፡፡ በህይወት ሂደት ውስጥ የተፈጠረና በዚሁ ሂደት ውስጥ እያደገ የሚሄድና በሥነምግባር የሚጠና የሰውልጅ የአስተሳሰብ ዘርፍ ነው፡፡

ፀረ-ሙስና፡- በሀገራችን አሁን ያለው የሥነምግባር ሁኔታ እንዴት ይገለፃል?

ዶ/ር ጠና ፡- አሁን ያለነው ጉራማይሌ ሁኔታ ዉስጥ ነው፡፡ በአንድ በኩል ከቀደመው ትውልድ የተላለፈለትን ግብረገባዊ እሴቶችን በመጠበቅና በማክበር እየኖረ ያለ በርካታ ህዝብ አለ፡፡ በዚህ ረገድ እውነትን መፈለግና ታማኝ መሆን፤ ተባብሮና ተከባብሮ መኖር መልካም የሆኑ ሥነ ምግባራዊ እሴቶች መሆናቸውን የሚረዱ ወገኖች አሉን ማለት ነው፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው በህዝቡ ውስጥ መልካምነት በተወሰነ ደረጃ መኖሩን ነው፡፡ ነገር ግን መልካምነትና ሥነምግባር በምንፈልገው መጠንና ዓይነት አላደገም፡፡ ለሀገራችንና ለታሪካችን የሚመጥን ግብረገባዊና ሥነምግባራዊ ሕይወትና ባሕል አልገነባንም፡፡ ይህን ከማድረግ አንጻር አሁንም የሚገባውን እያደረግን አይመስለኝም፡፡ ይህ ማለት ግብረገብና ሥነምግባር እየተወሳሰቡ በመሄድ ላይ ያሉ ችግሮቻችንን ለመቅረፍ በሚያስችል መልኩ የዳበረ አይደለም፡፡ በህዝባችን የዕለት ተዕለት ግንኙነትና ህይወት ውስጥ ቢኖርም የሚፈልገውን ያህል ጉልበትና ጥንካሬ የለውም፡፡ ስለዚህ የጊዜውን ጥያቄዎች የመመለስና የወቅቱን ችግሮች የመፍታት አቅም ያንሰዋል፡፡

ለዚህ አንዱ ምክንያት ደግሞ ግብረገብን በትምህርት ቤት ለረጅም ጊዜ ›ለማስተማራችን ነው፡፡ የእኛ ሀገር ትምህርት በአብዛኛው በምዕራባውያን ሥርዓተ-ትምህርት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ባብዛኛው ከዚያ ነው ተቀድቶ ወይም ተኮርጆ የመጣው ወይም የሚመጣው፡፡ እነርሱ ደግሞ ለግብረገብ ብዙም ትኩረት አይሰጡም፡፡ በተለያዩ መስኮች በተለይ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ያደረጓቸው ልማቶች ለግብረገብ ተገቢውን ትኩረት እንዳይሰጡ አድርጓቸዋል፡፡ በእርግጥ ይህ ልማት ግብረገብን ሊተካ የሚችል ባይሆንም የሚገባውን ትኩረት መነፈጉ እኛን የሚጎዳንን ያህል እነርሱን ለጊዜው ላይጎዳቸው ይችላል፡፡ በረጅም ጊዜ ሂደት ውስጥ ግን እጅግ አስከፊ የሆነ የስብዕና ቀውስ በእነርሱም ላይ ያደርሳል፡

በዚህ ሳቢያ እኛም ልክ እንደ ምዕራባውያን ለሌሎች የትምህርት ዓይነቶች እንጂ ለግብረገብ ትኩረት መስጠቱን ትተን ቆይተናል፡፡ በእርግጥ በአንዳንድ አገሮች ደግሞ ጠበቅ ያለ የሥነ ምግባር ትምህርት ሲሰጥ እናያለን፡፡ እኛ ግን በዘመናዊ ትምህርት ማስፋፋት ታሪካችን ውስጥ ከዚህ ውጪ ሆነን ነው የቆየነው፡፡ በዚህ ምክንያት ግብረገብነት ካለው አጠቃላይ የሰው ልጅ ዕድገት አንጻር እየወረደ መምጣቱ በግልፅ ይታያል፡፡ በትምህርት ቤት በዋነኛነት የምንማራቸው ሁለት ነገሮች ናቸው፡፡ እነሱም በሳይንስ የተረጋገጡ እውነቶች እና ከህይወት ተሞክሮ የተገኙ እሴቶች ናቸው፡፡ እኛ ሰዎች ሣይንሳዊ ትንታኔ ካለው እውነታ ይልቅ ግብረገባዊ ለሆኑ እሴቶች ቅርብ ነን፡፡

ስብዕናችን በአብዛኛው የሚሠራው በግብረገብ እሴት እንጂ በሣይንሳዊ እውነታ አይደለም፡፡ ይህ ማለት ግን ሳይንሳዊ እውነት ለህይወታችን ዋጋ የለውም ማለት አይደለም፡፡ የዚህ ዓይነቱ እውነትም የራሱ የሆነ አስተፅኦ አለው፡፡ ይሁን እንጂ የግብረገብ እሴት መልካምነትን እና እኩይነትን፣ትክክለኝነትንና ስህተትን ለይቶ በማውጣት ህይወት የሚመራበትን መርህ ይሰጣል፡፡ ሰው ምክንያታዊና ሰብአዊ ፍጡር በመሆኑ ግብረገብና ሥነምግባር በልዩነት ያስፈልጉታል፡፡ እኛ ግን ከህይወታችን ጋር ያን ያህል ቁርኝነት ያላቸውን ግብረገብና ሥነ-ምግባር አስፈላጊነትና ዋጋ እምብዛም አልተረዳንም፡፡ ለዚህ ነው ሥነ ምግባርንና ግብረገብን ዘላቂ በሆነ ሁኔታ በእኛነታችን ውስጥ ለመትከል ያደረግነው ጥረት አነስተኛ ሆኖ የቆየው፡፡

በእርግጥ አሁን አሁን በትምህርት ቤቶች ውስጥ የግብረገብ ትምህርት በመጠኑ እየተሰጠ መሆኑን እረዳለሁ፡፡ ያም ቢሆን የተባለው የግብረገብና የሥነምግባር ትምህርት እየተሰጠ ያለው ከአስፈላጊነቱና ከጠቀሜታው አንጻር መሆን የሚገባውን ያህል አይደለም፡፡ ትምህርቱን ለማስፋፋትና ለማጠናከር የሚያስፈልገውን ያህል በቂ ትኩረት አልተሰጠውም የሚል እምነት አለኝ፡፡ በዚህ ጉዳይ የተደበላለቀ ስሜት ነው ያለኝ፤ እየተሰጠ ያለው ትምህርት መልካምነትን በምንፈልገው መጠን ያዳበረ ስለማይመስለኝ፡፡ መጥፎውን ከጥሩ መለየት የተሳናቸውና ፍጹም ችግር ውስጥ ያሉ ዜጎችን እያየን ነው፡፡

ባለፈው ጊዜ የትምህርት ፍኖተ ካርታ ለውይይት ቀርቦ በነበረ ጊዜ ለዚህ የትምህርት መስክ ጠንከር ያለ ግምት እንዲሰጠው ምክክር ተደርጎ እንደ ነበር አስታውሳለሁ፡፡ ነገር ግን አሁን በፍኖተ-ካርታው መሠረት በአዲስ መልክ በተቀረጸው ሥርዓተ-ትምህርት ውስጥ ያለው ቅርጽና ይዘት በቀደመው ሥርዓተ-ትምህርት ውስጥ ከነበረው እምብዛም የተለየ አይደለም፡፡ ይህ ማለት አሁንም ማስተማር በሚገባን መጠን እያስተማረን አይደለንም፡፡ ስለዚህ አሳሳቢነቱ እንደቀጠለ ነው፡፡ የምርምር ስራዎችም በዚህ ላይ ትኩረት አላደረጉም፡፡ ለዚህ መስክ በነፈግነው ትኩረት መጠን የሚያስከፍለን ዕዳ አለ፡፡

እኛ እኮ ብዙ ችግሮች ያሉብን ህዝቦች ነን፡፡ የነበሩንን መልካም እሴቶች እንኳ ማስቀጠል አልቻልንም፡፡ ይህ በግብረገብ እና ሥነምግባር ትምህርት ዙሪያ በደንብ ያለመሥራታችን ውጤት ነው፡፡ በአግባቡ አላስተማርንም፤ ህዝቡ ውስጥ እንዲሰርፅ አላደረግንም፡፡ ባጭሩ በግብረገብ የታነፀ ትውልድ እንዲፈጠር ያደረግነው ጥረት በቂ አይደለም፡፡ ስናስተምር ሰዎች ወደ ውስጣቸው ወስደው የራሳቸው ያደርጉታል፤ ከዚያም በተግባራቸው ያንፀባርቁታል፡፡ የሥነ-ምግባር እና የግበረገብ ትምህርት ማንነትን የሚገነባ ስለሆነ ለሰብዓዊ ፍጡር በእጅጉ የሚያስፈልግ ነው፡፡

ከምንም በላይ እኛነታችን የሚታነፀው በግብረገብና በሥነምግባር ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ከማንኛውም ትምህርት በላይ ወይም ያልተናነሰ ለግብረገብና ሥነ-ምግባር ትምህርት ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል፡፡ በግብረገብ የታነፁ ወጣቶችን ካፈራን ሀገርን በአስተማማኝ መሠረት ላይ እንደማቆም ይቆጠራል፡፡ ይህ ካልሆነ ለወደፊቱ አሳሳቢ ችግሮች ይገጥሙናል፤ ነባር ችግሮችን ሳንፈታ አዳዲስ ችግሮች ይፈጠራሉ፡፡ በዚህ ዘመን ሉላዊነት (ግሎባላይዜሽን) እየገፋ የሚያመጣው ችግርም አለ፡፡ ያንን ችግር የመቋቋም አቅማችን

## ቆይታ

ደካማ ነው፡፡ እነዚህ ትምህርቶች ቢስፋፉ ኖሮ ግን ከውስጥ ያሉብንን ችግሮች ለመቀነስና ከወጪ የሚመጡትን ተፅዕኖዎች ለመቋቋም ብርቱ አቅም ይሆኑን ነበር፡፡

ፀረ-ሙስና፡- ኢትዮጵያውያን ኃይማኖተኞች ነን፡፡ በቤተክርስቲያናትም ሆነ በመስጊድ ግብረገባዊነት ይሰበካል፡፡ የሥነ-ዜጋና የሥነ-ምግባር ትምህርትም እየተሠጠ ነው፤ ግን ውጤቱ ብዙ አይታይም፡፡ ችግሩ ያለው የቱ ጋር ነው?

ዶ/ር ጠና፡- በእርግጥ ትምህርት በሰው ላይ የሚፈጥረው ለውጥ ወዲያው የሚታይ አይደለም፡፡ ትምህርት በሰው ላይ የሚያመጣው ለውጥ ውጤት ነው፡፡ ውጤት ደግሞ የሚታየው በተለያዩ ምክንያቶች የተለያዩ ጊዜያትን ፈጅቶ ነው፡፡ በእርግጠኝነት ለውጥ ያመጣል ወይም ውጤት አለው፡፡ ይሁን እንጂ በባሕርይው ምክንያት ትምህርት በተማሪው ላይ የሚያመጣውን ለውጥ በመጠንም ሆነ በጊዜ መለካት ያስቸግራል፡፡ በሌላ በኩል ሥነ-ዜጋ ሥነምግባር አለመሆኑን፤ ሥነ-ምግባርም ስነ-ዜጋ አለመሆኑን መረዳት ያስፈልጋል፡፡ አንዱ ችግራችን ስነ-ዜጋንና ሥነምግባርን መደበላለቅ ውዥንብር ይፈጥራል፡፡ ሁለቱም የየራሳቸው የሆኑ ባሕርያት አላቸው፡፡ ሁለቱን ባንድ ላይ በመጨፍለቅ የስነ-ዜጋና የሥነምግባር ትምህርት እንሰጣለን ማለት ለኔ የሚመች አይደለም፡፡ ስነምግባርን እያስተማረ ያለው ራሱ ማነው? ለመኖር መሥራትና ለስራው ትልቅነት ራስን ሰጥቶ መስራት የተለያዩ ነገሮች ናቸው፡፡ ሥነምግባርን ለማስተማር ማሟላት የሚኖርባቸው መስፈርቶች አሉ፡፡ በያገባኛል መንፈስ፣ በኃላፊነት ስሜት፣ በፅናትና ቅንነት ትውልድን ለመለወጥ አቋም ይዞ የሚሠራ ሰውና የዕለት ተግባሩን ለማከናወን ያህል ብቻ የሚሠራ ሰው ብርቱ ልዩነት አላቸው፡፡

ሥነምግባርን ማስተማር ራስን አርአያ አድርጎ ማቅረብን ይጠይቃል፡፡ አንድ ሰው ያልተገቡ ባህሪያት እያሳየ #ሥነምግባርን አስተምራለሁ$ ቢል የሚሰማው ሰው ማግኘት የሚችል መሆኑን እጠራጠራለሁ፡፡ የዚህ ትምህርት ዘርፍ አንዱ ተግዳሮት ይህ ነው፡፡ የራሱ የሆነ ሠው ወይም ባለሙያ ይፈልጋል፡፡ #እንጀራ እበላበታለሁ$ ብሎ ሣይሆን #ሰው አፈራበታለሁ፤ አገር የሚረከብ መልካም ዜጋ እፈጥርበታለሁ$ ብሎ ራሱን የሰጠ መምህር ይፈልጋል፡፡ ታዲያ እንዲህ ዓይነት መምህራን አሉን ወይ? ይህ አስቸጋሪ ጥያቄ ነው፡፡

ሌላው ይህንን ትምህርት የሚሰጠው መምህር ሥነምግባርን ወይም ግብረገብን በቅጡ ያውቀዋል? ይህም ሌላ ጥያቄና ችግር የሚፈጥር ጉዳይ ነው፡፡ ስንቶች ናቸው ከፍልስፍና ትምህርት ክፍል ወጥተው ወይም የሥነምግባር ትምህርት ወስደው ወደ ማስተማሩ የገቡት? አሁን ይህን ትምህርት የሚያስተምሩት አብዛኛዎቹ ከሌሎች የማህበራዊ ሣይንስ ዘርፎች የመጡ መምህራን ናቸው፡፡ እናም በዘርፉ በቂ ኮርሶችን ሳይወስዱ የሚያስተምሩ መምህራን ለሥነምግባር እና ግብረገብ ትምህርት የሚሰጡት ትኩረት ምን ያህል ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡ እራሳቸው የመጡበት የትምህር ዘርፍ ይስባቸዋል፡፡ ስለዚህ የግብረገብና የሥነምግባር ትምህርት በአግባቡ እየተሰጠ ነው ብዬ አላምንም፡፡

በሌላ በኩል በነበረው ሥርዓተ-ትምህርት ውስØ ሥነ ምግባር የሥነ-ዜጋ ተቀጣይ ተደርጎ ነው የቀረበው፡፡ የሥነምግባር ትምህርትን በሥነ-ዜጋ ውስጥ ማስተማርና የሥነ-ዜጋ ትምህርትን በሥነምግባር ውስጥ ማስተማር በፍፁም የተለያዩ ነገሮች ናቸው፡፡ ለሥነ-ዜጋ መሠረቱ ራሱ ሥነምግባር ነው፡፡

በኃይማኖት በኩል ያለውን ስንመለከት ድሮ ህዝቡ ለሀይማኖት ትምህርት ዋጋ ይሠጣል፡፡ እንደሚታወቀው አንድ ዘመን አልፎ ሌላ ዘመን ሲመጣ በሂደት ውስጥ በርካታ ነገሮች ይለዋወጣሉ፡፡ የሰዎች አተያይና አስተሣሠብ ይለወጣል፡፡ በተለይ ደግሞ በዘመነ ደርግ ለሀይማኖት የተሠጠው ትኩረት አናሳ ስለነበረ በዚያ ምክንያት ብዙ ነገር ተዘበራርቋል፡፡ በሌላ በኩል በኃይማኖት ተቋማት ላይም የሚታዩ ችግሮች አሉ፡፡ ይህም ትምህርቶቹ ፍሬ እንዳያፈሩ ምክንያት ሳይሆኑ አይቀርም የሚል እምነት አለኝ፡፡ የሃይማኖት ተቋማቱ ራሳቸው በግብረገብ አንጻር ድሮ በነበሩበት ሥፍራ ላይ ናቸው? እኔ እጠራጠራለሁ፡፡ በእርግጥ ለሀይማኖታቸው ታማኝ፣ በበጎ ተግባራቸው

**አብዛኛው ተናጋሪ የሚለውን አያደርግም። የምናስተምረውን የምናደርግ ቢሆን፤ የምንፅፈውን ወደ ተግባር መለወጥ ብንችል፤ ትውልዱን በአግባቡ ለማነፅ እና ሀገራችንን ወደፊት ለማራመድ አንቸገርም ነበር። በተግባር እና በቃል መካከል ልዩነት ስላለ የተሟላ ሥነምግባር ያለው ትውልድ ለመፍጠር ተቸግረናል።**

ለምዕመኑም አርአያ የሆኑ የሀይማኖት አባቶች አሁንም አሉ፡፡ በተቃራኒው በዚህ ዘመን ኃያል በሆነው ገንዘብ ቁጥጥር ሥር የወደቁትንም እናያለን፡፡ #ስንቶቹ አባቶች ናቸው ለእምነታቸው ራሳቸውን ሰጥተው በማገልገል ላይ ያሉት;$ የሚለውን ጥያቄ በአግባቡ ማጤን ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም በሥነምግባር ዙሪያ የሚሠጠው የግብረገብ ትምህርት በሚፈለገው መጠን ስኬታማ ነው ማለት አይቻልም፡፡ #አታድርግ$ እና #አድርግ$ ማለት ብቻውን እኮ ውጤት አያመጣም፡፡ መምህራኑ ምሳሌ ሆነው መታየት ይኖርባቸዋል፡፡ እኔ አትዋሽ ካልኩህ፤ እኔ ውሸት ከመናገር የታቀብኩ መሆኔን ማረጋገጥ አለብኝ፡፡ ስለዚች ሀገር ልማት፣ ዕድገት ብዙ እናወራለን፤ መሬት የሚወርደው ግን ጥቂት ብቻ ነው፡፡ አብዛኛው ተናጋሪ የሚለውን አያደርግም፡፡ የምናስተምረውን የምናደርግ ቢሆን፤ የምንፅፈውን ወደ ተግባር መለወጥ ብንችል፤ ትውልዱን በአግባቡ ለማነፅ እና ሀገራችንን ወደፊት ለማራመድ አንቸገርም ነበር፡፡ በተግባር እና በቃል መካከል ልዩነት ስላለ የተሟላ ሥነምግባር ያለው ትውልድ ለመፍጠር ተቸግረናል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ በትክክል እያስተማርን አይደለም፡፡ ሲቀጥል በምናስተምረውና በተግባር በምንፈፅመው መካከል ብዙ ልዩነት አለ፡፡ ይህ ደግሞ ታች ወርዶ ዜጎችን መቅረፅ በሚገባን መልክ መቅረፅ አላስቻለንም፡፡

ፀረ-ሙስና፡- በትምህርት ተቀባዩ አካልስ የሚስተዋል ችግር አለ ብለው ያስባሉ? የግሎባላይዜሽንና የቴክኖሎጂ እድገቱ ተፅዕኖስ እንዴት ይታያል?

ዶ/ር ጠና፡- የተሰጣቸውን ትምህርት ሰምተው፤ ወደ ዕውቀት ለውጠውና በተግባር የተፈተኑ ሰዎች ቁጥራቸው ይህን ያህል አይደለም፡፡ ይህ በራሱ ውስብስብ ችግር ነው፡፡ ይህን ችግር ለማለፍ በሚያስችል መልኩ ትምህርቱን ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ ክፍል ውስጥም ይሁን በኃይማኖታዊ ሥፍራዎች የምናስተምረው መልካም ነገርን ነው፡፡ በዓለም ላይ በተጨባጭ የሚታየው ደግሞ በአብዛኛው የዚህ ተቃራኒ ነው፡፡ ትውልዱ መልካም ነገሮች ከሚማራቸው ቦታዎች ሲወጣ የሚያየው ብልጭልጭ ነገሮችን ነው፡፡ በዚህ በቀላሉ የሚሸነፉ አሉ፡፡

እንደሚታወቀው ትክክለኛ መንገድን መምረጥ ሁሉን እርከኖች በስኬት ማለፍ ያስችላል፡፡ ዛሬ ብዙ አቋራጭ ነገር ግን ትክክል ያልሆኑ መንገዶች አሉ፡፡ ትውልዱ ደግሞ ቀለል ያሉ መንገዶችን ይፈልጋል፡፡ በትክክለኛ መንገድ ላይ ካለው ተግዳሮት ጋር ትግል መግጠም አይፈልግም፡፡ ያለ ልፋት፤ ያለ ውጣ ውረድ የሚፈልገውን ማግኘት ይመኛል፡፡ ይህን የተማረው በአንድ በኩል ከሚኖርበት ህብረተሰብ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ቴክኖሎጂ ከፈጠራቸው ነገሮች መማር አለ፡፡ ትውልዱ በአካባቢው በአቋራጭ የከበሩ ሠዎች ሲደነቁና ሲሞካሹ ይመለከታል፡፡ ያላቸውን ደስታና ምቾት ያያል፡፡ ይኼኔ በክፍል የተማረውን ወይም ከኃይማኖት ተቋማት ያገኘውን ትምህርት እንደቀልድ (ውሸት) በማየት የስህተቱን መንገድ ይመርጣል፡፡ በዚህም ምክንያት በጣም ጥቂቶቹ ናቸው በተማሩት መሠረት ሲጓዙ የሚገኙት፡፡ ዞሮ ዞሮ ግን በተሻለ መንገድ ጠንክሮ በማስተማርና ለመልካም ነገር አርአያ በመሆን ይህን ፈተና ማለፍ የሚጠበቅ ነው፡፡

ለዚህ ሁሉም የሚመለከታቸው ወገኖች ተቀናጅተው መሥራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በተወሰኑ አካላት ላይ የሚጣል ኃላፊነት አይደለም፡፡ እንደ ሀገር በጣም የተቀናጀ ሥራ መሠራት ይኖርበታል፡፡ በውል የተጠና፣ ዓላማ ያለውና እርስ በርሱ የሚደጋገፍ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ሥርዓት በሀገር ደረጃ መኖር አለበት፡፡ በሀገራችን ያሉ ጠቃሚ እሴቶችና ትውፊቶች ተለይተው ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው፡፡ እነዚህ ሁሉ ተደራጅተውና ተቀናጅተው ወደተግባር ሲገቡ ከየትኛውም አቅጣጫ የሚመጣውን አሉታዊ ግፊት የመቋቋም አቅም ይዳብራል፡፡ አለበለዚያ ከውጪ የሚመጣው አፍራሽ ግፊት በአንድ በኩል ሾልኮ ሊገባ ȷችላል፡፡ የተገነባውንም ያፈርሳል፡፡ እኛ ሀገር አንዱ የሚገነባ ነው፤ ሌላው ደግሞ የሚያፈርስ ነው፡፡ ለምን አንድ ላይ መቆም፤ መደማመጥና መናበብ እንደሚያቅተን አይገባኝም፡፡

በአንድ በኩል ለኔ ብቻ የሚል ዝንባሌ አለ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ እንደሀገር የመቆም ፍላጎት አለ፡፡ ይህንን ማስታረቅ የሚያስችል ሁኔታ መፈጠር አለበት፡፡ የለበጣ ወይም የሴራ ሥራ ሣይሆን ሁሉም በቅን ልቦና ተቀራራቢ ወደ ሆኑ ሀሣቦች በመምጣት ትውልድን የሚታደግ ሥራ መሥራት ያስፈልጋል፡፡ ለዚህ የሚሆን ፖሊሲም የሚያስፈልግ ይመስለኛል፡፡ ይህም ሆኖ ሁሉም ሰው አንድ ይሆናል ብዬ አላስብም፡፡ ቢያንስ ቢያንስ ግን እያንዳንዱ ሰው ምክንያታዊ መሆን ቢችል የሀገርን ፍላጎት፣ የህዝብን ፍቅር እና ክብር ከግንዛቤ ያስገባ ውሳኔ መወሰን ይችላል፡፡ ይህን ማድረግ ካልተቻለ ግን ከውጪ የሚመጣውን ግፊትና ከውስጥ የሚነሳውን ችግር መቋቋም ያስቸግራል፡፡ ሁሉም የራሱን ብቻ ሣይሆን የሌላውንም እያየ የጋራ የሆነ መሠረት መገንባት ይኖርበታል፡፡

ፀረ-ሙስና፡- ለነዚህ የሥነምግባር ችግሮች መስፋፋት ምክንያቱ ምንድን ነው?

ዶ/ር ጠና፡- የራስ-ወዳድነት፤ ደንታ-ቢስነት፤ ተንኮልና የመሳሰሉት እኩይ ነገሮች መስፋፋት፤ ለመስኩ ተገቢውን ትኩረት መንፈግ፤ሀገር በቀል የሆኑ እውቀቶችና ክህሎቶችን አለመጠቀምና ሀገር በቀል በሆኑ እሴቶች አለመገልገል እንደ ምክንያት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ በግብረገብ መስክ እኛ ያለንን ብናስፋፋና ብናዘምን ብዙ ችግሮቻችንን መቅረፍ እንችል ነበር፡፡ አሁን አሉን የምንላቸው የስነምግባር እሴቶች ራሳቸው በአግባቡ ቢያዙ ትውልዱን በተሻለ መስመር መምራት የሚያስችሉ ናቸው፡፡ ይህ ባለመሆኑ ለሥነምግባር ችግሮች መስፋፋት ተጋልጠናል፡፡ ከልክ ያለፈ ራስ ወዳድነትና ስግብግብነት እየተስፋፋ ነው፡፡ ይህ በራሱ ለሥነምግባር ችግር መስፋፋት ሌላው ምክንያት ነው፡፡ ለሙስና መንሰራፋትም የራሱ የሆነ ትልቅ ድርሻ አለው፡፡ የተሠጠህን ኃላፊነት ተገን አድርገህ፤ የህዝብ ቋንቋ እየተናገርክ፤ የተገኘውንና የማይገባህን ሁሉ ለራስህ ብቻ የምታግበሠብስ ከሆነ ግዙፍ የሥነምግባር ችግር ለመኖሩ ማረጋገጫ ነው፡፡ ውሸት፣ ማጭበርበር፣ ማታለል፣ ሴራና ሸፍጥ መሥራት ሁሉ ከልክ ባለፈ ራስ ወዳድነት ውስጥ ይገለፃሉ፡፡ የራስ ያልሆነን ንብረት ለራስ ለማድረግ መታገል ኢግብረገብ ነው፡፡

ራስ ወዳድነት የሚያሳድርባቸውን ጫና መቋቋም ተስኗቸው በሥርቆት፣ በምዝበራና በውሸት ውስጥ የተዘፈቁ በርካቶችን እንታዘባለን፡፡ በገበያ ውስጥ ለጤንነት ጎጂ የሆኑ ነገሮች ከምግብ ነክ ነገሮች ጋር ቀላቅሎ መሸጥ ከልክ ያለፈ ራስ ወዳድነት ያመጣው ችግር ነው፡፡ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት የሚደረግ መሯሯጥ ችግሮች እንዲስፋፉ ምክንያቶች ሆነዋል፡፡ በእርግጥ በእጃችን ላይ ያለችውን ነገር ተካፍሎ ለመብላት ወይም ያለንን ለማካፈል የምናሳየው ፍላጎት መልካም ከሚባሉት የሥነምግባር እሴቶቻችን አንዱ ነው፡፡ ግን ደግሞ ለምን አብረን ሠርተን አብረን ማደግ እንደተሳነን ማሰብ ይኖርብናል፡፡ በበኩሌ የሥነምግባር ችግሮች የተስፋፉት በግብረገብ ትምህርት ላይ ብዙ አለመሰራቱ አንድ ትልቅ ምክንያት ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡ ሌሎች ብዙ ምክንያቶችም አሉ፡፡

ፀረ-ሙስና፡- ድህነትን ለሥነምግባር ችግሮቻችን ምክንያት ማድረግ እንችላለን?

ዶ/ር ጠና፡- ለምን በድህነት እናሳብባለን ድህነት የሰው ስራ ውጤት ነው፡፡ ኢትዮጵያ ምንም ያጣች ሀገር አይደለችም፤ በአግባቡ ብንጠቀምበት በቂ የተፈጥሮ ሀብት ባለቤቶች ነን፡፡ ግን ያለንን ማክበርና መጠቀም ተስኖን በድህነት እጅ የወደቅነው፡፡ በዚህ ላይ የበጎ አስተሳሰብ ችግሮች አሉብን፤ በህብረት መቆም ይቸግረናል፡፡ ዕውቀታችንን በአግባቡ ብንጠቀምና ተግባብተን በህብረት መቆም ብንችል ይህችን የመሰለች ሀገር ይዘን ለከፋ ችግር አንዳረግም ነበር፡፡ ቀና የሆነ አስተሳሰብ ከውስጣችን እየጠፋ መምጣቱ ብርቱ የግብረገብ ችግራችን ነው፡፡

ከራሳችን ምድር የተነሱ ገንቢ ዕውቀቶችንና አስተሳሰቦችን ለመጠቀም ፈቃደኞች አይደለንም፡፡ ያሉንን በጎና ጠቃሚ የሆኑ ነገሮችን ለይተን ማወቅ ይቸግረናል፡፡ ሁል ጊዜ ከሌሎች መቅዳት ነው የምንፈልገው፡፡ በእርግጥ ጠቃሚ ዕውቀቶች ማመንጨት ካልቻልን ከሌሎች መቅዳት ራሱ ጠቃሚ ነው፡፡ ግን የራሳችንን እርግፍ አድርገን በመተው መሆን የለበትም፡፡ የራሳችንን በተውን ቁጥር ግብረገባዊና ሥነ ምግባራዊ እሴቶቻችን እየተሸረሸሩ ይሄዳሉ፡፡ አንዳንዴ ሀሳብን ከውጪ ማምጣት የሚፈለገው እዚህ ያለውን ችግር ለመፍታት ሳይሆን ገዥዎች ህዝብን በማደናገር የአገዛዝ ዘመናቸውን ለማራዘም የሚገለገሉበት

“ባሉብን የሥነምግባር... ወደ ገፅ 9 የዞረ



## ሳይቃጠል በቅጠል

# በሙስና ሥጋት ጥናት የተቋማት የሙስና ተጋላጭነትን መቀነስ



በሀገራችን በርካታ የመንግሥት እና የግል ተቋማት አገልግሎታቸውን እና ምርታቸውን በነፃም ይሁን በክፍያ ይሰጣሉ፡፡ አገልግሎት ፈላጊ ማህበረሰብም አገልግሎቱን በጥራት፣ በፍጥነት እና ግልፅነት ባለው መንገድ እንዲያገኝ ይጠብቃል፡፡

በሀገራችን የሚገኙ ተቋማትም አብዛኛውን ጊዜ የሚሰጡት አገልግሎት ግልጽነት የጎደለው፣ ተገቢውን ጥራት ያላሟላ እና ፍጥነት የሚጎድላቸው ናቸው፡፡ አገልግሎት ፈላጊው ዜጋ የሚፈልገውን አገልግሎት ለማግኘት ወደ ተቋም ሲሄድ የሚፈልገው አገልግሎት የት እንደሚገኝ፣ አገልግሎቱን ለማግኘት ምን ማሟላት እንዳለበት፣ አገልግሎቱን ማን እንደሚሰጠው፣ ለአገልግሎቱ ምን ያህል ክፍያ እንደሚፈጽም ማወቅ ይፈልጋል፡፡ ተቋማትም ይህን የዜጋውን ፍላጎት ለማሟላት የሚሰጡ አገልግሎቶችን የሚያሳዩ መረጃዎችን በሚታይ ቦታ መለጠፍ ወይም የዜጎች ቻርተር በማሳተም ማሠራጨትና ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ምርት እያመረተ የሚሸጠው ተቋም ደግሞ ስታንዳርዱን የሚያሟሉ ጥራት ያላቸውን ምርቶች በማምረት ለተጠቃሚ ያቀርባል፡፡

ከላይ የጠቀስናቸው አገልግሎት ሰጪ እና ምርታቸውን የሚሸጡ ሁለቱም ዓይነት ተቋማት ውስጥ ሙስና ይፈፀማል፡፡ የአገልግሎት ሰጪ ተቋም ውስጥ የሚሰጠውን አገልግሎት በማወሳሰብ ወይም ለሚሰጠው አገልግሎት ተፈላጊ የሆኑ መስፈርቶች ላይ የሌለውን መሥፈርት በማካተትና አገልግሎት ፈላጊውን በማሳመን የግል ኪስ ማደለብ፣ ተፈላጊው መስፈርት ተሟልቶ ላልቀረበ ጉዳይ የአገልግሎት ጥያቄን እንደምክንያት በመጠቀም ጉቦ መጠየቅ፣ አገልግሎት ላለመስጠት ሀሰተኛ ምክንያት በማቅረብ ጉቦ እንዲሰጥ መጠየቅ፣ ዜጋው አገልግሎት በሚፈልግበት ሰዓት ከሥራ ቦታ ላይ በመጥፋት አገልግሎት ፈላጊው ሳይፈልግ በአስገዳጅ ሁኔታ ጉቦ ወይም ምልጃ እንዲሰጥ ማድረግ ይገኙበታል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ተቋሙ ለሥራ የሚፈልጋቸውን ጉዳዮች ለማሟላት ግዥ ሲፈጽም የተፈለገውን የዕቃና የአገልግሎት ጥራት በማጓደልና ዋጋን በማጋነን ወይም ከተፈላጊው ዕቃ በላይ ግዥ እንዲፈጸም በማድረግ ሙስና ይሰራበታል፡፡ ይህ ዓይነት ድርጊት በአምራች ድርጅቶች ውስጥም የሚፈፀም ተግባር ነው፡፡ የተቋሙን አገልግሎት ለዘመዶቻቸውና ለጓደኞቻቸው ጥቅም በማመቻቸት ከዘርፉ ከሚገኘው ጥቅም ተጋሪ መሆን ከሌብነቱ ውስጥ አንዱ ነው፡፡

ከዚህ ዉጪ የተሰጠውን ኃላፊነት በመጠቀም የተቋሙን ንብረት በተጭበረበረ ዘዴ ለራስ መውሰድ ወይም ሠነዶችን በመደለዝና የሀሰተኛ ሠነድ በማዘጋጀት ገንዘብ ወጪ ማድረግ በተቋማት ከሚፈጸሙ የሙስና አይነቶች መካከል የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

በተቋማት ውስጥ ሙስና እንዲከሰት መንስኤ የሚሆኑ ሶስት ነገሮች አሉ፡፡ የመጀመሪያው አመለካከት ነው፡፡ በተፈጥሮ ራስ ወዳድ የሆነና የሞራል ዝቅጠት ያለው ሰው ሁልጊዜ በሥራ ሳይሆን በሌብነት መክበርን የሚያምን በመሆኑ ለሙስና አእምሮውን በማሳመን አልሞና አቅዶ የሚንቀሳቀስ ነው፡፡

ሁለተኛው አጋጣሚ ነው፡፡ አጋጣሚን በመጠቀም ሙስና የሚሠራ ሰው የህግና የመመሪያ ወቅታዊ አለመሆንን፣ የክትትልና የግምገማ ሥራ ጠንካራ አለመሆንን፣ ለሚያከናውነው ሥራ የሌሎች ሚና አለመኖርን፣ ውሳኔዎች በአንድ ሰው ብቻ የተሰጠ መሆኑን በመረዳት እንዲሁም በዝምድና፣ በጋብቻ፣ በሃይማኖትና በዘር የጥቅም ግጭት ትስስር በመፍጠር ሙስናን ይሰራል፡፡

ሶስተኛው የሰዎችና የሁኔታዎች ግፊት ነው፡፡ በተለይ እርጥብ የሥራ አካባቢ የሚሠራ ሰው በጓደኛ ወይም በቤተሰብ ወይም ወጪ ከገቢ በላይ ሲሆንበት ባይፈልግ እንኳን በግፊት በሙስና ይዘፈቃል፡፡ በመሆኑም በሚሠራው የሥራ አካባቢ በሁለተኛ ተራ ቁጥር በተገለፀው መሠረት ባያስብም ሠነዶችን በማጭበርበር ወይም ከሌሎች ግብረአበሮች ጋር በመተባበር ወይም በግሉ ወይም ለሥራ የወሰደውን ሀብትና ንብረት ይሰርቃል፡፡

ከላይ የተገለፁት የሙስና መንስኤዎች በሀገራችን ዘመናትን ያስቆጠሩና በየሥርዓቱ ተፈፃሚ የሚደረጉ በመሆናቸው ለሀገር እድገትና ሰላም ተግዳሮት ሲሆኑ ቆይተዋል፡፡ በዚህ ሌብነት ድርጊት ቀላል ግምት የማይሰጣቸዉ የተቋማት አመራርና ሠራተኞች ተሳታፊ ሲሆኑ አንዳንድ ባለሀብቶችና ደላሎችም ተጨማሪ አባባሽ ሞተሮች ናቸው፡፡

ሙስና በመንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት ውስጥ የሚፈጸም ዓለም አቀፋዊ ችግር ነው፡፡ ስለሆነም የተባበሩት መንግስታት ሀገራት የሙስና መከላከል ስምምነት በመፈጸም ትግሉን የጋራ እንዲያደርጉ አድርጓል፡፡ የአፍሪካ ህብረትም በተመሳሳይ የሙስና ችግርን በጋራ ለመታገል የአፍሪካ ሀገራት ስምምነት ፈጽማዋል፡፡

ሀገራችንም የተባበሩት መንግስታት የፀረ ሙስና ስምምነት ከመፈረሟ በተጨማሪ ሁለቱንም ስምምነት የሀገሪቱ ህግ አድርጋ በማጽደቅ የትግሉ ተሳታፊ መሆኗን አረጋግጣለች፡፡ ይህን ትግል የሚያስተባብረው ደግሞ የፌዴራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በማቋቋም በተግባር አሳይታለች፡፡ ተቋሙም በሥነምግባር ትምህርት ሙስናን የሚጠየፍ፣ የሚታገልና የሚከላከል ህብረተሰብ የመፍጠር፣ በተቋማት ውስጥ ሙስና እና ብልሹ አሠራር ለመፈጸም የሚያስችሉ አሠራሮችን በጥናት በማሻሻል ግልጽነትና ተጠያቂነትን ማስፈን፣ የሙስና ወንጀል ጥቆማዎችን በመቀበል፣ በመመርመር፣ በማስቀጣት፣ የተመዘበረ ሀብት የማስመለስ ሥራዎች ላይ ትኩረት አድርጎ ሲሰራ ቆይቷል፡፡

የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በህግ የተሰጡትን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት ላለፉት ሃያ አንድ ዓመታት ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ ይህ ተግባርና ኃላፊነት በሁሉም ክልሎች በተመሳሳይ በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡ በተቋማት ውስጥ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎችን በደንብ ቁጥር 144/2000 በማደራጀት ሥነምግባር የማስተማር፣ ሙስና እና ብልሹ አሠራር የመከላከል እንዲሁም የሙስና ወንጀል ጥቆማዎችን የመቀበልና ለፍትህ አካላት የማስተላለፍ ሥራዎችን በመሥራት ላይ ናቸው፡፡ የሙስና እና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ሥራ አካል የሆነውን የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ሥራን በህግ በማስደገፍ ተመራጮች፣ ተሿሚዎችና የሚመለከታቸው የመንግስትና የመንግስት የልማት ድርጅት ሠራተኞች ሀብትና ንብረት እንዲያስመዘግቡ አድርጓል፡፡

ኮሚሽኑ በአዋጅ ቁጥር 235/1993 ዓ/ም ይዞት ከተቋቋመባቸው ዓለማዎች ውስጥ በሶስተኛነት የተቀመጠውንና የሙስና ወንጀል ጥቆማዎችን በመቀበል፣ በመመርመር፣ በማስቀጠት፣ የተመዘበረ ሀብት የማስመለስ ሥራ መንግስት በፍትህ ዘርፍ ለዜጎች የአንድ መስኮት አገልግሎት ለመስጠት ባስቀመጠው አቅጣጫ መሠረት በአዋጅ ቁጥር 943/2008 ለፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽንና ለፍትህ ሚኒስቴር እንዲዛወር ተደርጓል፡፡

ከዚህ ውጪ ግን የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና መከላከል መርህ ላይ የተመሠረተ ተግባርና ኃላፊነት ተሰጥቶት በተቋማት ውስጥ ለሙስና እና ብልሹ አሠራር ተጋላጭ የሆኑ አሠራሮች ላይ በራሱ አቅም እና በተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች አማካይነት የአሰራር ሥርዓት ጥናት በማካሄድ የማሻሻያ ሀሳቦች ተግባራዊ እንዲሆኑ ክትትልና ግምገማ በማካሄድ ያረጋግጣል፡፡ ይህ ሥራ ተቋማት ለሙስና እና ብልሹ አሠራር ተጋላጭ የሆኑ አሠራሮች ላይ ግንዛቤ ወስደው ማሻሻያ ለማድረግ የሚረዳቸው ስለመሆኑ በቅጡ ካለመረዳት ለጥናት ሥራ ወደ ተቋማት ሲኬድ አለመተባበር ይስተዋላል፡፡ በጥናት የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦችን ለመተግበር ፈቃደኛ አለመሆን እንደተግዳሮት የሚወሰድ ነው፡፡ በኮሚሽኑ በኩል ደግሞ ለተቋም የሙስና እና ብልሹ

## ሳይቃጠል በቅጠል

አሠራር የመከላከል ሥራው በቂ ዕውቀትና ልምድ ካለመያዝ የተነሳ በተቋማት እየታየ ያለውን የሙስና እና ብልሹ አሠራር በትክክል ለመለየት አለመቻልና በቀላሉ ተተግብሮ ሙስና እና ብልሹ አሠራር ለመከላከል የሚያስችል የማሻሻያ ሀሳብ ለማቅረብ የአቅም ማነስ የሚታይበት ነው፡፡ በመሆኑም በተቋማት በሚፈለገው ደረጃ የሙስና እና ብልሹ አሠራር ችግሮች እየተቀረፉ አይደለም፡፡

በመሆኑም በርካታ ተገልጋይ ባላቸው ተቋማት ውስጥ ለዜጋው ፍትሃዊ የሆነ አገልግሎት ባለመሰጠቱ ለእንግልት በመዳረግ በመንግስት አገልግሎት ላይ እሮሮና ቅሬታ በማሰማት ላይ ይገኛሉ፡፡ ጥቂቶች በሌብነት ከብረው የተንደላቀቀ ኑሮ ሲኖሩ ብዙኃኑ ዜጋ ደግሞ የልማት ተጠቃሚ እየሆነ አይደለም፡፡ በሙስና የከበሩ ሰዎች የሀገሪቱን ሠላም ከመንሳት ጀምሮ በርካታ ተግባራትን እየፈፀሙ ህብረተሰቡን ለበርካታ ችግሮች እየዳረጉ ናቸው፡፡

ስለሆነም ኮሚሽኑ ቀደም ሲል የነበረበትን የሙስና ችግር ለመቅረፍ እንዲያስችለው በ2014 በጀት ዓመት በሪፎርም አዲስ አደረጃጀትና አሠራር በማዘጋጀትና የሰው ኃይል አቅም በመገንባት ዓለም አቀፍ ተሞክሮ የሆነውን የዘርፍ ተኮር የሙስና ሥጋት ጥናት በማካሄድና የማሻሻያ ዕቅድ በማቅረብ ተቋማት የሙስና ሥጋት ቅነሳ ስትራቴጂ በማዘጋጀት እንዲተገብሩ ለማድረግ ሥርዓት ዘርግቶ ወደ ትግበራ ገብቷል፡፡

የሙስና ሥጋት ጥናት የሚካሄደው በቅድሚያ ሥራውን ለመሥራት በሙስና መከላከል ሥራ ላይ ልዩ ዕውቀትና ልምድ ያለውን ባለሙያ፣ በቅድሚያ ለሙስና ጥናት ሥራው የመረጃ ምንጭ የሚሆኑ የተቋም ህጎች፣ የአሰራር መመሪያዎች፣ ድርጅታዊ መዋቅር በመሳሰሉት ላይ በቂ ግንዛቤ መያዝና ለሥራው የሚያስፈልግ ሀብት ዝግጅት ማድረግን የሚጠይቅ ነው፡፡ ተግባሩ ለሥራ ምቹ ሁኔታን ከመፍጠር የሚጀምር ሲሆን ጥናት ሥራው ላይ በተቋሙ ሥራ ላይ ቆይታ ያለቸው በቂ ልምድና ዕውቀት ያላቸው አመራርና ሠራተኞች በግልጽ ማሳተፍንም ይጠይቃል፡፡ የተቋሙ የሙስና ሥጋት ልየታ በኋላ ለሙስና ሥጋቶች ደረጃ መስጠት እና እንደ የደረጃቸው የማሻሻያ ዕቅድ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ በማሻሻያ ዕቅዱ መሠረት የሙስና ሥጋት ቅነሳ ስትራቴጂ ማዘጋጀትና መተግበር ግድ የሚል ይሆናል፡፡

የሙስና ሥጋት መከሰት መንስኤው በተቋሙ ውስጥ የአሰራር መመሪያ ግልጽ ባለመሆኑ ወይም በባለሙያዎች ዘንድ የሥራ ክፍፍል አለመኖር፣ ህግ ወቅታዊ ባለመሆኑ፣ የክትትልና ቁጥጥር ማነስ፣ ሙስናን ለመከላከል የአመራር ቁርጠኝነት ማነስና የመሳሰሉት ክፍተቶች ናቸው፡፡ የሙስና ወንጀል እንዳይፈፀም ቀድሞ ለመከላከል እንዲያስችል ለሙስና ሥጋት የሆኑ አሠራሮችን በመለየትና ለሥጋት ያለቸውን ደረጃ በማስቀመጥ የማሻሻያ ዕቅድ ለማቅረብ የሚከናወን ሥራ ነው፡፡

የሙስና ሥጋት ጥናት ማለት ሙስና ሊፈጸም የሚችልባቸውን አሠራሮችንና አደረጃጀቶችን በመለየት የመከላከል ሥራ መሥራት ነው፣ ሥራው በተቋም ሙስና ስለመፈጸሙ ፍተሻ ወይም ሙስና የፈጸመ ሰው መለየት ወይም ሙስና ስለመፈጸሙ መረጃ መፈለግ አይደለም፡፡ ለሙስና ሥጋት ሊሆን የሚችል ወይም ሙስና ለመፈጸም ዕድል ሊፈጥር የሚችል አሰራርና አደረጃጀት በግልጽ መለየትና ቀድሞ ማሻሻያ ለማድረግ የሚያግዝ ነው፡፡

የሙስና ሥጋት ጥናት በሀገር ደረጃ ወይም በዘርፍ ወይም በተቋም ደረጃ ሊፈጸም የሚችል ነው፡፡ በሀገር ወይም በዘርፍ ደረጃ በመሥራት ወደ ተቋም ማውረድ ወይም በተቋም ደረጃ መሥራት ይቻላል፡፡ ሥራው በተቋም አደረጃጀት፣ አሠራርና በሂደት ላይ ያተኮረ ሊሆን ይችላል፡፡ የሙስና ሥጋት ጥናት ትርጉም ከሙስና ትርጉም ተያይዥነት ያለው ሲሆን ሙስና ሊፈጽምባቸው ምቹ ሁኔታ (ጉቦ ለመቀበል፣ ለመዝረፍ፣ ለማጭበርበር፣ ለመስረቅ) ምቹ ሁኔታ ሊፈጥሩ የሚችሉ አደረጃጀቶችን፣ አሠራሮችንና ሂደቶችን ያካትታል፡፡

የሙስና ሥጋት ጥናት ሥራ ሶስት ደረጃዎች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያው ችግሩን ለይቶ ወዲያው ማከም ነው፡፡ በዚህ አሠራር ተቋሙን አደረጃጀት፣ መዋቅር፣ በሥራ ላይ ያሉ ህግ፣ ደንብና መመሪያዎች ላይ ያሉ ክፍተቶች ለሙስና ምቹ ሁኔታን የሚፈጥሩ ስለመሆናቸው በመለየት በወቅቱ ማሻሻልና ምንጩን መድፈን ነው፡፡ ይህ ክፍተት በአጭሩ የሚለየው በተቋሙ በሚካሄዱ የሙስና ቅኝት ጥናቶች፣ በተጨባጭ በተፈጸሙ ሙስና ወንጀሎች መነሻነት ወይም በተቋሙ ውስጥ ሲከሰት ከነበረው ልምድ በመነሳት ሊሆንም ይችላል፡፡

ሁለተኛው የሙስና ሥጋት አካባቢዎች በዳሰሳ ጥናት መለየት እና የሙስና ሥጋት የመሆን እድልና ሊያስከትል ከሚችል ጉዳት መጠን ጋር በማስላት በሚገኝ ውጤት መነሻነት በተቋሙ የታዩ የሙስና ሥጋት የሆኑ አሠራሮችን ከፍተኛ፣ መካከለኛና ዝቅተኛ ደረጃን መስጠት ነው፡፡ ሶስተኛውና የመጨረሻው ለሁለቱም የሙስና ቅነሳ ሥራዎች የሙስና ሥጋት መከላከያ የማሻሻያ ዕቅድ ማቀድ ሲሆን ዕቅዱ የነበረውን የቁጥጥር ሥርዓት ማጠናከር ወይም አዲስ የቁጥጥር ሥርዓት መንደፍ ነው፡፡ ካልሆነም ደግሞ የነበረውን አሠራር ሙሉ ለሙሉ በማስቀረት በአዲስ አሠራር መተካት ነው፡፡

የሙስና ሥጋት ጥናት ምንጮች የሠነድ መረጃ የመጀመሪያው ሲሆን ሁለተኛው በተቋሙ ሥራ በቂ ዕውቀትና ልምድ ላላቸው አመራርና ሠራተኞች ቃለ መጠይቅ በማካሄድና በተለያዩ የሙያ ስብጥርና ኃላፊነት ደረጃ ላይ ያሉ ሰዎች ያካተተ የተናጠልና የቡድን ውይይት በማካሄድ የሚገኝ መረጃ ነው፡፡

በሙስና ሥጋት ጥናት የሚቀርበው የማሻሻያ ዕቅድ በተቋሙ በራሱ አቅም የሚተገበር ወይም በሌላ የውጭ አካል ዕገዛን የሚጠይቅ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለሆነም በማሻሻያ ዕቅዱ ላይ ለተቋሙ የበላይ አመራር፣ ለሌሎች የሥራ ኃላፊዎችና ለባለድርሻ አካላት ግንዛቤ መፍጠር እና በትግበራ ሂደት ላይ የባለድርሻ አካላት ሚናቸውን እንዲወጡ ከማድረግ ባሻገር የመተግበሪያ ጊዜ ገደብን በማስቀመጥ አፈፃፀሙን ትኩረት በመስጠት መከታተልና መገምገም አስፈላጊ ነው፡፡ ለዚህም የተቋም አመራር ቁርጠኝነትን የሚጠይቅ ሲሆን በማሻሻያ ዕቅዱ ትግበራ ላይ በሙያው ዕውቀትና ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች እንዲሳተፉ ማድረግንም ይጠይቃል፡፡

ለአብነት ያህል ኮሚሽኑ በ2014 በጀት ዓመት ካካሄዳቸው የሶስት ዘርፍ ተኮር የሙስና ሥጋት ጥናቶች ውስጥ ፍርድ ቤት አንዱ ነው፡፡ ይህ ጥናት የተካሄደው በሀገር ደረጃ በጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ በከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ በመጀመሪያ ደረጀ ፍርድ ቤት፣ በሸሪያ ፍርድ ቤት እና በዳኞች አስተዳደር ጉባኤ መሥሪያ ቤቶች ላይ ሲሆን በጥናቱ የፌዴራል፣ የኦሮሚያ፣ የደቡብ ክልላዊ መስተዳደሮች የተመረጡ ጠቅላይ ፍርድ ቤትና ወረዳ ፍርድ ቤቶች ተካትተዋል፡፡ በሂደቱም የተመረጡ ዳኞችና የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች ተሳትፈዋል፡፡ በጥናቱ ከሰነድ፣ ከመጠይቅና ከቃለ-መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች ጥቅም ላይ ዉለዋል፡፡ በዘርፉ የሚታዩ የሙስና ሥጋቶችን የመከሰት ዕድልና ቢከሰት ሊያጋጥም ከሚችለው ጉዳት ስሌት አንፃር ደረጃ የመስጠትና የማሻሻያ ዕቅድ የማቅረብ ሥራ ተከናውኗል፡፡

## ከሙስና ምርመራ ዘገባ ማህደር

# የሙስና ወንጀል ምርመራ፣ የክስ እና አለም አቀፍ የትብብር ስራዎች

የሙስና ወንጀል የሚፈጸመው የአፈጻጸሙን ሂደትና ሥልት እንዳይደረስበት በማድረግ በከፍተኛ ጥናት፣ ጥንቃቄና ሚስጢር የሚፈጸም ወንጀል ነው፡፡ ስለዚህ የወንጀሉ አፈፃፀም ወይም ስለመፈጸሙ የሚጠቁም መረጃ ለማግኘት አዳጋች በመሆኑ ከሌሎች ከተለመዱ ወንጀሎች የተለየና ውስብስብ ያደርገዋል፡፡ ሌላው ለጉዳዩ ባለቤት ነኝ ባይ የሚል አለመኖሩም የሙስና ወንጀልን ከሌሎቹ ወንጀሎች የሚለየው ነው ፡፡ በዚህም የሙስና ወንጀል የሚያደርሰው ጉዳት በአንድ ወይም በተወሰነ ቤተሰብና ግለሰብ ላይ የሚወሰንና በቀጥታ የሚታይ ሳይሆን አገርንና ህዝብን በሙሉ የሚያጠቃልል መጠነ ሰፊ ነው፡፡ ይሁንና የተፈጸመውን ወንጀል የማጋለጥ ወይም የመታገል ሀገራዊ ግዴታ አለብኝ፣ እንደ ዜጋ ይመለከተኛል በማለት ጉዳዩን ለህግ የሚያቀርብ ሰው በጣም ጥቂት ነው፡፡ ጥቆማ ቢቀርብም እንኳ ጠቋሚ በሆነው አካል ላይ የዛቻ፣ ማስፈራራት፣ ከስራ ቦታ ማፈናቀል፣ከደረጃ ዝቅ ማድረግ እንዲሁም የአካል እና የሕይወት ጉዳት ይደረሳል የሚል ስጋት ከመኖሩ ባሻገር ጠቋሚ የሆነውን አካል እንደአላዋቂ በመመልከት ገለልተኛ የመደረግ ሁኔታ የሚስተዋል በመሆኑ ሙስናን እንደሌሎች ወንጀሎች የመዋጋትና የመከላከል ትግሉን ሙሉ ሲያደርገው አይስተዋልም፡፡

የሙስና ወንጀል ምርመራ እጅግ ፈታኝ መሆኑ ደግሞ ከሌሎች ወንጀሎች ውስብስብ የሚያደርገው የወንጀል አፈፃፀም ነው፡፡ የሙስና ወንጀልን የሚፈጽሙት ሰዎች አስቀድሞ በተጠናና በረቀቀ ዘዴ በተቀነባበረ መንገድ ራሳቸውን አደራጅተው፣ ስልቶችን በጥንቃቄ ነድፈው፣ ከተጠያቂነት ማምለጥ የሚችሉበትን መንገድ ሁሉ ቀድመው አመቻችተው በመሆኑ ወንጀሉን የተለየ ውስብስብና ረቂቅ ባህሪ እንዲኖረው አድርጎታል፡፡ ከዚህም ባሻገር ሙስና ፈጻሚዎቹ የመወሰን አቅምና ሥልጣን ስላላቸው ምርመራ/የመከላከል ስራው እንዳይካሄድ በማደናቀፍ ሂደቱን እንዲዘገይ የማድረግ፤ምርመራው ቢካሄድም ልፍስፍስ እንዲሆን በማድረግ የተጠርጣሪዎችን የተጠያቂነት ደረጃ ማሳነስ ወይም ነፃ እንዲወጡ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣ የተጀመረን ምርመራም እንዲኮላሽ ማድረግ ሲሳናቸው ደግሞ መርማሪውን/ባለሙያውንም ሆነ ከምርመራው ጋር ግንኙት ያላቸውን ግለሰቦች በተለያየ መንገድ ማጥቃት ወይም ማስጠቃት ፣ ከዚህ በተጨማሪ ሙስናን የሚመረምረውንና የሚከሰውን አካል እራሱ በሙስና እንዲዘፈቅ በማድረግ ወንጀሉን የመከታተልና የማጋለጥ ሥራ የተለየ፣ ውስብስብና ረቂቅ ባህርይ እንዲላበስ ያደርገዋል፡፡

ሀገራት የተለያዩ የሙስና መከላከል ሞዴሎችን ይጠቀማሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ፡-

የሙስና መከላከል እና የህግ ማስከበር ሞዴል/ሁለገብ ሞዴል / Multi Purpose Anti Corruption Model or The Universal Model/ አንዱ ሲሆን ይህን አይነት ሞዴል "የሶስት ጦር ውጊያ ስልት" እየተባለ የሚጠራ ሲሆን ሙስናን በብቃት ለመዋጋት ህዝብ በሙስና ላይ እንዲዘምት ማስተማር እና ማስተባበር፣ የሙስና መከላከል ዘዴዎች (የህግ እና የአሰራር ማሻሻያዎች) ተግባራዊ በማድረግ እና በሙስና ላይ የተሳተፉ አካላትን ተጠያቂ ለማድረግ (በመርመር) ነው፡፡

ይህን ሞዴል የሚከተሉ ሀገሮች የመከላከል፣ የመመርመር እና የመክሰስ ሰልጣን ለአንድ ተቋም በመስጠት ውጤታማ እና የተቀናጀ የፀረ ሙስና ትግሉ እንዲኖር ያግዛል የሚል እምነት አላቸው፡፡ በእንደዚህ አይነት አደረጃጃት የተከማቸ ስልጣን እንዳይፈጠር፣ የዕርስ በርስ የቁጥጥር /የcheck and balance/ ስርዓት እንዲኖር በተወሰነ መልኩ የክስ ስራ ከፀረ ሙስና አደረጃጀቱ ነፃነት ተሰጥቶት እንዲሰራ /እንዲደራጅ/ የሚደረግበት አግባብ አለ፡፡ እዚህ ላይ ሊሰመር የሚገባው ጉዳይ ግን ይህን አይነት ሞዴል የሚከተሉ አገሮች ቢያንስ የምርመራ ስራ በፀረ ሙስና ተቋም ውስጥ እንዲደራጅ የሚያደርጉበት ሁኔታ አለ፡፡ ይህን አይነት የፀረ ሙስና ሞዴል የሚከተሉት አገሮች በዋናነት የሚታወቁት ለረዥም ጊዜ በሙስና ተዘፍቀው የነበሩ/ያሉ/፣ የመንግስት ተቋማት ህግ አስከባሪ አካላት (Law enforcement institutions) ጭምር በሙስና የሚጠረጠሩበት እና የሙስና ሰለባ የሆኑበት፣ በተነፃፃሪ በኢኮኖሚ እድገት ወደ ኋላ የቀሩ፣ የዳበረ የዴሞክራሲ ባህል የሌላቸው እና ዝቅተኛ የመንግስት የእርስ በርስ የቁጥጥር /Check and Balance/ ስርዓት የነበራቸው/ያላቸው/ አገሮች ናቸው፡፡

ለምሳሌ ይህን ሞዴል ከሚከተሉ አገሮች ውስጥ ሆንግ ኮንግና ቻይና ("Independent Commission Against Corruption")፣ሲንጋፖር ("Corrupt Practice Investigation Office") እና ቦትስዋና ("Directorate on Corruption and Economic Crime") በሚል ተቋሞቻቸውን በመሰየም የሚንቀሳቀሱ እንደሆነ በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ በተለይም በአፍሪካ ቦትስዋና የፈጠረችው የፀረ ሙስና ተቋም

## ከሙስና ምርመራ ዘገባ ማህደር

ለሌሎች አርአያ የሚሆን ተቋም ሲሆን በአፍሪካ ሙስናን በመታገል የተሻለች አገር ሆና እንደተቀመጠች የሀገራትን የፀረ ሙስና ኢንዴክስ በየአመቱ ይፋ የሚያደርገው "ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል" እየተባለ የሚጠራው አለም አቀፍ ድርጅት ካወጣው መረጃ ለመረዳት ይቻላል፡ ፡ የህግ የማስከበር ሞዴል /Law Enforcement Model/ ደግሞ ሌላኛው ሲሆን ይህ አይነቱ ሞዴል ደግሞ ሀገራት ሙስናን ለመታገል የሚያስችላቸው በዋናነት በምርመራ እና ክስ ላይ ያተኮሩ ሲሆኑ ይህን ስራ ለመስራት በተለመደው የህግ ማስከበር ስርዓት ማለትም በፖሊስ እና ዓቃቤ ህግ ተቋማት እንዲሰራ የማድረጊያ ሞዴል ነው፡፡

በዚህ ሞዴል ውስጥ አንዳንድ አገራት "ልዩ ዲፓርትመንት" (special department) በማቋቋም የሚታገሉበት ሁኔታ ያለ ሲሆን የዚህ ሞዴል ውጤታማነት እንደየሀገሩ ሁኔታ ይለያል፡፡ ለምሳሌ በታዳጊ አገሮች የሚገኙ የፖሊስ እና የአቃቤ ህግ ተቋማት ነፃ እና ጠንካራ ከአሰፈፃሚ አካል ጣልቃ ገብነት የፀዱ ባለመሆናቸው ውጤታማ አይደሉም፡ ፡ እንዲያውም እንዲህ አይነት አደረጃጀት "እንዳያማህ ጥራው፣ እንዳይበላ ግፋው" እንደሚባለው አይነት አባባል መንግስት ሙስና መታገል አይፈልግም የሚለውን ሀሜት ለማስወገድ የሚያደራጀው እንጂ መንግስት ከልቡ ሙስናን ለመዋጋት ፍላጎት ስላለው አይደለም የሚያቋቁመው በሚል በስፋት የሚተችበት ሁኔታ አለ፡፡

የአደጉ አገሮች በገነቡት ጠንካራ የዲሞክራሲ ባህል፣ የግልፅነት ስርዓት እንዲሁም በሂደት በአገኙት ልምድ ታግዘው ሙስናን ጨምሮ በተወሰነ ወንጀል ላይ ትኩረት ሰጥተው የሚሰሩበት እና ውጤታማ የሆኑበት ሁኔታ አለ፡፡ ለምሳሌ እንግሊዝን ለአብነት ማንሳት ይቻላል፡፡

ሆኖም ግን ይህን ሞዴል የሚከተሉ አገሮች የሙስና መከላከል ስራን ከህግ ማስከበር ስራው (ከምርመራ እና ክስ ስራ) ጋር አጣምረው ስለማይሰሩ በተለይም ታዳጊ በሆኑ አገሮች የተቀናጀ የፀረ ሙስና ትግል በማድረግ በኩል ችግር ያለባቸው እና ህዝብን ሞብላይዝድ የማድረግ አቅማቸው አነስተኛ ትኩረት የሚሰጡበት ሁኔታ ስለአለ ውጤታማ አይደሉም፡፡

ለምሳሌ ኖርዌይ ("The Norwegian National Authority for Investigation and Prosecution of Economic and Environmental Crime") ፣ እንግሊዝ ("Metro Politian Police Anti Corruption Command)፣ ኬንያ ("Anti Corruption Commission") እና ደቡብ አፍሪካ ("The Special Investigation Unit of South Africa" for the Reparation of Corruption) በምሳሌነት የሚጠቀሱ አገሮች ናቸው።

### የምርመራና ክስ ስራዎች

ሙስናን የመከላከልና እርምጃ የመውሰድ ስራ አንዱ አካል የሆነው የህግ ማስከበር ስራ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ባለፉት ዓመታት ካከናወነቻቸው እና እያከናወነችው ካለው ተግባራት አንዱ የሙስና ወንጀል ምርመራና ክስ ስራ ነው፡፡

በዚህ ረገድ ከሙስና ወንጀል ጥቆማ ጋር በተያያዘ ለኮሚሽኑና ለተለያዩ የፍትህ አካላት የተለያዩ ጥቆማዎች ቀርበዋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ የሙስና ወንጀል ምርመራ ማድረግ፣ በምርመራው መሰረት የክስ ስራዎችን ማከናወን ፣በሙስና ምክንያት የተመዘበረ የመንግስት ሀብትና ንብረት ለመንግስት እንዲመለስ የማድረግ ስራ፣ ለጠቋሚዎች የህግ ጥበቃና ከለላ የመስጠት ስራ እና በሙስና ወንጀል ክስ ስራ ጋር በተያያዘ ተከሳሾችን የመርታትና ጥፋተኛ የማሰኘት አቅም በመዝገብና በተከሳሽ ውጤት ማስመዝገብ ነው፡፡

በዚህ ረገድ በርካታ ስራዎች የተከናወኑ ሲሆን ከሙስና ወንጀል ምርመራ ጋር በተያያዘ 91,103 የሙስና ወንጀል ጥቆማዎች ቀርበው የነበረ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ 67,729 የሚሆኑት በኮሚሽኑ የህግ ስልጣንና ተግባር ስር የሚወድቁ የነበሩ ሲሆን ቀሪ 23,374 ከኮሚሽኑ ስልጣንና ተግባር ውጭ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ የሙስና ወንጀል ምርመራ በማድረግ ረገድ 43,211 ጥቆማዎች ላይ ምርመራ ተደርጎ በ14,489 መዝገቦች ላይ ክስ እንዲመሰረት ተደርጓል፡፡ በ12,285 ተከሳሾች ላይ ደግሞ የክስ ፋይል እንዲከፈት ተደርጓል፡፡

በዚህ የፍርድ ሂደት በ12,183 የክስ መዝገቦች ላይ ውሳኔ ሲሰጥ በ10,508 የክስ መዝገቦች ላይ ለኮሚሽኑ ሲወሰን በ10,284 ተከሳሾች ላይ ለኮሚሽኑ የጥፋተኝነት ውሳኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ በዚህም የኮሚሽኑ በፍርድ ጥፋተኛ የማሰኘት አቅም በመዝገብ 86.25% ሲሆን በተከሳሽ 83.71% ነው፡፡ በዚሁ የክስ ሂደት በፍርድ ቤት የተጣለው የወንጀል ቅጣት መጠን ከፍተኛው 25 ዓመት ፅኑ እስራት ሲሆን ዝቅተኛው ደግሞ 3 ወር ቀላል እስራት ነበር፡፡ የገንዘብ ቅጣትን በተመለከተ ከፍተኛው ብር 70,000 ፤ዝቅተኛው ደግሞ ብር 200 ነበር፡፡

ከሙስና ወንጀል ምርመራ ስራ ጋር የሚያያዘው ሌላው ጉዳይ ለወንጀል ጠቋሚዎችና ምስክሮች የህግ ከለላና ጥበቃ ማድረግ አንዱ የነበረ ሲሆን በዚህም 1,894 የሚሆኑ የህግ ከለላ ይሰጠኝ ጥያቄ ቀርቧል፡፡ ከዚህ ውስጥ ለ517 ከለላ ጠያቂዎች ከለላ ሲሰጥ 165 ለሚሆኑት ደግሞ ከለላ የሚያሰጥ ሆኖ ባለመገኘቱ ከለላው ሊሰጥ ያልቻለ ሲሆን 12 ጉዳዮች ደግሞ በወቅቱ በመጣራት ላይ የነበሩ ናቸው፡፡

በያዝነው በ2014 ዓ.ም በጀት ዓመት የሙስና መረጃን ከቅበላ እስከ ውሳኔ ያለውን አስተዳደር ተግባራዊ ለማድረግ ታቅዶ በዚሁ መሰረት 2,681 ጥቆማዎችን በመቀበልና በመተንተን ሙስና እና ብልሹ አሰራር ሆነው የተገኙ ጉዳዮችን በመለየት ለሚመለከታቸው ተቋማትና የፍትህ አካል መፍትሄ እንዲያገኙና ውሳኔ እንዲሰጥባቸው እንደተደረገ ማየት ይቻላል፡፡

### 1.1. ለመንግስት የተመለሰ ሀብትና ንብረትን በተመለከተ

ኮሚሽኑ ከሙስና ወንጀል ምርመራና ክስ ስራ ጋር በተያያዘ በሙስና ወንጀል የተመዘበረ ሀብትና ንብረት ለማስመለስ ባደረገው እንቅስቃሴ ባለፉት ዓመታት ውስጥ ዋና ዋና የሆኑ በርካታ በሙስና የተመዘበረ ገንዘብ፣መሬት፣ ቤት እና የንግድ ድርጅቶችን በማስመለስ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን የተደረገ ሲሆን ከብዙ በጥቂቱ ዋና ዋናዎቹ 1,264,299,553.2 የኢትዮጵያ ብር፣1,050,000.00 ከመኖሪያ ቤት ሽያጭ የተገኘ፣ 2,052,500.00 ከተሽከርካሪ ሽያጭ የተገኘ፣259,000.00 ከሼር የተገኘ፣ 2,680,317.43 ብር ከፍርደኞች የተሰበሰበ ቅጣት፣ 96 ኪሎ ግራም ወርቅ፣321 መኖሪያ ቤት፣ድርጅትና ህንፃዎች፣385.77 ሔክታር መሬት፣40.97 ሔክታር የእርሻ መሬት፣ 39.54 ሔክታር የእርሻ ኢንቨስትመንት መሬት፣40 መኪና፣ 69 ሞተር ሳይክል፣16,119 ቶን ፌሮ ብረት የሆኑ ንብረቶች ለመንግስት እንዲመለሱ ተደርጓል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ከፍትህ ሚኒስቴር በተሰበሰበ መረጃ መሰረት፡-

- ንብረት ማስመለስን በተመለከተ ሰባት መቶ ሚሊዮን ብር ለመንግስት ተመላሽ መሆኑን፤
- ከመንግስትና ከግል ባንኮች የተመዘበረ ሁለት መቶ ሚሊዮን ብር ለመንግስት ተመላሽ መደረጉን፣
- በጥሬ ገንዘብ 88,332,878.43 ብር፣ በንብረት 86,239,828.47 የሚገመት የተለያዩ ንብረቶች፣ የገንዘብ ግምቱ 1.4 ሚሊዮን ብር የሆነና 400 ካሬ ሜትር ቤት፣1,999 ካሬ ሜትር ቦታ፣

በሌላ በኩል በተጨማሪ መረጃ ብር 9,773,676.00 (ዘጠኝ ሚሊዮን ሰባት መቶ ሰባ ሶስት ሺህ ስድስት መቶ ሰባ ስድስት ብር) በዋናነት ለመንግስት ተመላሽ እንደተደረጉ መጥቀስ ይቻላል፡፡

### የሙስና ወንጀልን ለመከላከል አህጉር አቀፍ እና አለም አቀፍ የትብብርና የቅንጅት ስራዎች

ከላይ በክፍል አንድ እንደተገለፀው ኢትዮጵያ አህጉር አቀፍና አለም አቀፍ የፀረ ሙስና ትግሎችን በመቀላቀል የተለያዩ ስራዎችን ያከናወነች ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ እ.ኤ.አ ህዳር 26/2007 በአዋጅ ቁጥር 544/2007 የተባበሩት መንግስታት የፀረ ሙስና ኮንቬንሽንን በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፅድቃለች፡፡

ሀምሌ 11/2003 በሞዛምቢክ ዋና ከተማ ማፑቶ የፀደቀውን የአፍሪካ ህብረት የሙስና መከላከያ እና መዋጊያ ኮንቬንሽንንም በተመሳሳይ መልኩ በአዋጅ ቁጥር 545/2007 በፓርላማ በማፅደቅ የሀገሪቱ የህግ አካል እንዲሆን ተደርጓል፡፡

በእነዚህ ሁለት አዋጆች መሰረት ሀገሪቱ የተባበሩት መንግስታትና የአፍሪካ ሕብረት የፀረ ሙስና መከላከልና መዋጊያ ኮንቬንሽኖችን አፈፃፀም በኮሚሽኑ አስተባባሪነት የተለያዩ ተግባራት እንደተከናወኑ ማየት የሚቻል ሲሆን በዚህ ረገድ ኮሚሽኑ እ.ኤ.አ. ከፌብርዋሪ 23 እስከ 26 2015 በተካሄደው የአፈፃፀም ግምገማ መሰረት ኢትዮጵያም በኮንቬንሽኑ የገባቸውን ግዴታ ለመወጣት ባለባት ግዴታ መሰረት እ.ኤ.አ. ከ2010-2015 (ከ2003 እስከ 2008 ዓ.ም) ያለውንና በኮንቬንሽኑ ምዕራፍ 3 የሙስና ወንጀልን ወንጀል አድርጎ በመደንገግ በቅጣት እና ህግ ማስከበር (Criminalization and law enforcement articles 44-50), በምዕራፍ አራት አለምአቀፍ ትብበርን (International Cooperation) አስመልክቶ የአፈፃጸም ሪፖርት አቅርባ በቶጎ እና በማልታ እንደተገመገምች መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡

በዚህም በኮሚሽኑ አስተባባሪነት ከፀረ ሙስና ትግሉ ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ሚና ያላቸውን ፍትህ ሚኒስቴር፣ ፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን፣ የፋይናንስ መረጃ ማዕከል፣የፌደራል ፍርድ ቤቶች፣ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ፣ የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር፣ የሲቪል ማህበረሰብ ተወካዮች በተገኙበት ግምገማው ተከናውኗል፡፡

2ኛው ዙር የኮንቬንሽኑ አፈፃፀም ግምገማ ጋር በተያያዘ በተባበሩት መንግስታት የፀረ-ሙስና ኮንቬንሽን ምዕራፍ ሁለት በሙስና መከላከል (Corruption perevention) እና በምዕራፍ አምስት በሙስና የተመዘበረ ሀብትን በማስመለስ (Asset recovery) ረገድ ያከናወነቻቸውን ተግባራት ገምጋሚ ለሆኑት ኮንጎ ብራዛቪል እና ግሪክ ለማቅረብ ሪፖርቱን በማጠናቀቅ ለሚመለከተው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በመላክ ለግምገማ ስራዎች ዝግጅት እየተደረጉ ሲሆን አፈፃፀሟ በዚሁ አግባብ እንደሚገመገም ይጠበቃል፡፡

ሌላው በፀረ ሙስና ኮንቬንሽኑ አንዱ ዋና ጉዳይ የሆነው ዓለም አቀፍ ትብብር ሲሆን በዚህ ረገድ የሙስና ወንጀል ፈፅመው የተጠረጠሩ ወይም የተፈረደባቸው ሆነው ወደ ሌላ ሀገር የሸሹ ወይም የተጠለሉ የሀገሪቱ ዜጎች ሲኖሩ ተላልፈው እንዲሠጡ/Extradition/ ስምምነት ማድረግ ነው፡፡

ኢትዮጵያ በኮንቬንሽኑ አንቀጽ 44 ላይ በአሳልፎ መስጠት ላይ ሪዘርቬሽን የነበራት ቢሆንም ኮሚሽኑ ከተለያዩ የመንግስት ተቋማት ጋር በመስራት ባደረገው የጋራ እንቅሰቃሴ ይህንን ተዓቅቦዋን በግንቦት ወር 2013 ዓ.ም ሙሉ ለሙሉ በማንሳት ለኮንቬንሽኑ አፈፃፀም ያላትን ሙሉ ቁርጠኝነት እንዳነሳች ከመረጃዎች መረዳት ይቻላል፡፡

በዚህ መሰረትም የሙስና ወንጀል ፈፅመው የተጠረጠሩ ወይም የተፈረደባቸው ሆነው ወደ ሌላ ሀገር የሸሹ ወይም የተጠለሉ የሀገሪቱ ዜጎች ሲኖሩ አስልፈው እንዲሠጧት/Extradition/ መጠየቅ እንደምትችል በ2004 በወጣው የወንጀል ህጋችን አንቀፅ 11፣ 12 እና 21 ላይ በግልፅ ተደንግጓል፡፡

በዚህ መሰረት ከጅቡቲ እና ከየመን ጋር አስላፎ መስጠትን የሚመለከት ስምምነቶችን አድርጋለች፡፡ እንዲሁም የኢትዮጵያ ዜግነት የሌላቸው ሆነው የውጭ ሀገር ዜጎች የወንጀል ህግን በመተላለፍ ሀገሪቱ ላይ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ ተላልፎ እንዲሰጣት ልትጠይቅ እንደምትችል በወንጀል ህጋችን አንቀፅ 21 ላይ ተደንግጎ ይገኛል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ኮሚሽኑ ኢትዮጵያን በመወከል ህግ ከማስፈፅም ጋር የተያያዙ ስምምነቶችን በአህጉር አቀፍ ደረጃ ያደረገ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ the Eastern Africa Police Chiefs Cooperation Organization (EAPCCO), INTERPOL, Asset Recovery Inter Agency Network for Eastern Africa (ARIN-EA) and the StAR/INTERPOL Asset Recovery Focal Points network፣ የአፍሪካ የፀረ ሙስና ማህበር (Africa Association of Anti-Corruption Authorities) የተባሉ ስምምነቶችን እንዲፈረሙ ተድርጓል፡፡ በዚህም ኮሚሽኑ ሀገሪቱን በመወከል በሚደረጉ ስብሰባዎችና ግንኙነቶች ላይ በመገኘት የሚጠበቅበትን ኃላፊነት እየተወጣ ይገኛል፡፡

### በሙስና የተመዘበር ሃብትን ማስመለስና ማስተዳደርን በተመለከተ

ኢትዮጵያ ህግ ከማስፈጸም ጋር የተያያዙ ስምምነቶችን የሚመለከቱ "the Eastern Africa Police Chiefs Cooperation Organization (EAPCCO)", "INTERPOL", "the Asset Recovery Inter Agency Network for Eastern Africa (ARIN-EA)" and the StAR/INTERPOL Asset Recovery Focal Points network" የተባሉ ስምምነቶችን አድርጋለች፡፡

ኢትዮጵያ ከሌሎች ሀገሮች ጋር አሳልፎ መስጠትን የተመለከተ ስምምነት ባይኖራትም በተግባር ግን በተለይ የወንጀል ፍሬ ሆኖ ከሀገር የተሰወረ ወይም የሸሸ ገንዘብን ለማሳመለስ የምታደርገው ጥረት እንዳለ መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡

በሙስና እና በሌሎች ልዩ ልዩ ምክንያቶች ከሀገራችን የተመዘበረ እና የሸሸ በርካታ ገንዘብ እና ሃብት እንዳላት ይነገራል፡፡ ይህን ሃብት ለማስመለስ በአለው የዲፕሎማሲ ግንኙነት ጥረት የተደረገ ቢሆንም በልዩ ልዩ ምክንያት እስካሁን አጥጋቢ ውጤት አልተገኘም ማለት ይችላል፡፡ ከሙስና ወንጀል ክስ ስራዎች አፈፃፀም ጋር በተያያዘ፣

- ከሀገሪቱ በሙስና ተዘርፎ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ብር አንድ መቶ ሰላሳ ቢሊዮን ብር እንደሚገኝ ተጠቁሟል፡፡ (የኤፌዴሪ ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ የ2012 ዓ.ም የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት)

ከዚህ አኳያ ሙስናን በተቀናጀና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመዋጋት በሀገር ውስጥ ከሚደረገው ጥረት ባሻገር በአህጉር ደረጃ መደጋገፍ እጅጉን አስፈላጊ ነው፡፡ የሀገርን ሀብትና ንብረት የሚመዘብሩ ግለሰቦችና ድርጅቶች የሀብታቸውን ምንጭ ለመደበቅና የሚያመቻቸው ጊዜና ቦታ ህጋዊ አስመስለው ለመጠቀም እንዲሁም ከተጠያቂነት ለማምለጥ ከሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች መካከል አንዱ የሀገርን ሀብት ዘርፈው ወደ ሌላ ሀገር መኮብለል ነው፡፡

የሀገርን ሀብት ዘርፈው የሚኮበልሉትን እነዚህን ግለሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች ህግ ፊት አቅርቦ ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኙ ለማድረግ፤ የተዘረፈው ሀብት እንዲከበርና በመጨረሻም ወደ መጣበት ሀገር እንዲመለስ ለማድረግ አካባቢያዊና አህጉራዊ ትብብር አስፈላጊ ከመሆኑም በላይ እያንዳንዱ ዜጋ በዚህ ረገድ የሚጠበቅበትን ከሀገር ስለሸሸ የህዝብ ሀብት የሚያውቀውን መረጃ በመስጠት የዜግነት ድርሻውን እንደሚወጣ ሙሉ እምነት አለን፡፡

## ቆይታ

# “ባሉብን የሥነምግባር...

ከገፅ 5 የቀጠለ

ስልት ይመስላል፡፡ እዚህ ሀገር ውስጥ ያለው አስተሳሰብና ዕውቀት በአግባቡ ከተያዘ ህዝባችንን የሚለውጥና የሚያሳድግ ነው፡፡ ከውጪ የመጡትን ሞክረን ብዙም አልተሣካልንም፡፡ እነርሱ በልካቸው ሰፍረው የሠሩትን ለእኛም ዕድገት እንዲያመጣልን ሞክረናል፡፡ የፈለግነውን ውጤት ግን አላገኘንም፡፡ ይህንን ችግር ተረድተን ከራሳችን ሕዝብና ምድር የሚመነጭ መፍትሄ ማግኘት ካልቻልን የድህነታችን አንዱ ምክንያት ሆኖ መቀጠሉ የግድ ይሆናል፡፡

ኢትዮጵያ ደሃ አይደለችም፤ እኛ ነን ደሃ ያደረግናት፡፡ ከማንኛውም ሀገር ያላነሰ የተፈጥሮ ሃብት አላት፡፡ ዋናው ድህነታችን የአስተሣሠብ ነው፡፡ የሥራ ሥነምግባር የለንም፤ ማለት የስራ ባሕላችን ጠንካራ አይደለም፡፡ ስለዚህ ድህነትን ያመጣነው እኛ ነን፡፡ እጃችን መሥራት የሚገባውን ነገር አልሠራም፡፡ አእምሯችን ማሰብ በሚገባው ልክ አላሰበም፡፡ ብቻውን ተፈጥሮና ቆሞ የሚሄድ ድህነት የለም፡፡ በሰው ሥራ ውስጥ የሚገለፅ ድህነት ነው ያለው፡፡ ይህ ደግሞ የራሳችን ድክመት ነው፡፡ የኛ ስንፍና ነው፡፡ ድህነት አንዱ የሥነምግባር ጉድለት መገለጫ እንጂ ለሥነምግባር ችግር ዋና ምክንያት ሊሆን አይችልም፡፡

ፀረ-ሙስና፡- በሀገር ደረጃ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ ለመጣው ለዚህ የሥነምግባር ችግር ማን ኃላፊነቱን ይውሰድ?

ዶ/ር ጠና፡- ሁላችንም ኃላፊነት አለብን፡፡ እኔም ኃላፊነት አለብኝ፡፡ አንተም፤ እናንተም፤ እነርሱም፤ ሁላችንም የዚህች ሀገር ልጆች ነን፡፡ ስለዚህ በሀገራችን ውስጥ እየተባባሰ የሚሄደውን የሥነምግባር ችግር የመፍታት ኃላፊነት አለብን፡፡ የሙስና መሐንዲሶችና ሰለባዎችም እኛው ነን፡፡ ሙስና በከፋ መልኩ እየተስፋፋ የመጣው በሥነ-ምግባር ዝቅጠት ምክንያት ነው፡፡ ልጆቼን እንዴት ነው ያሳደኳቸው? ሥነምግባርና ግብረገብ ምን እንደሆኑና ምን ዋጋ እንዳላቸው አሳውቀአቸዋለሁ? አንተስ? አንቺስ? ሌላውስ? ህብረተሰቡስ ልጆቹን እንዴት ነው የሚንከባከባቸው? ለእርስ በእርስ ግንኙነትስ የሚሠጠው ዋጋ እንዴት ይገለፃል? ለሌላው የሚያሳየው ክብርስ...? ትምህርት ቤቶች ምን እየሰሩ ነው? መንግስትስ ሥነምግባር የተላበሱ ዜጎች እንዲፈጠሩና እንዲኖሩ ምን እያደረገ ነው?

እነዚህ ሁሉ በሀገር ደረጃ ሥነምግባርን የተላበሰ ትውልድ እንዲፈጠርና እንዲጎለብት ብርቱ አስተዋፅኦ አላቸው፡፡ አልፎ አልፎ «አያገባኝም» የሚል አስተሣሠብ ይደመጣል፡፡ በእኛ ሀገር እንዲህ ማለት አያዋጣም፡፡ ምክንያቱም አኗኗራችን የጋራ ነው፤ ሀገርም የጋራ ናት፡፡ ሁሉም ሠው በእኔ ውስጥ አለ፡፡ እኔም በሁሉም ውስጥ አለሁ፡፡ በዚህ ሁኔታ እንዴት አያገባኝም እላለሁ፡፡ ሁሉም በየደረጃው ያገባኛል ማለት አለበት፡፡ በተወሰኑ ወገኖች ብቻ የሚሠራ ሥራ ለውጥ አያመጣም፡፡ በስፋት ህዝብን ማስተማርና ማሳተፍ ያስፈልጋል፡፡

ፀረ-ሙስና፡- ሙስናን ለመከላከል ሥነምግባርን ማስፋፋት በፌደራልና በክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና አስተባባሪነት ትምህርት ለመስጠት ጥረት ይደረጋል፡፡ በዚህ ላይ እርሶ ምን አስተያየት አለዎት?

ዶ/ር ጠና፡- ሙስናን የሚጠየፉ ዜጎችን፣ ሥርዓትና መንግሥት መፍጠር፤ በሌላ በኩል በግብረገብና በሥነ-ምግባር የተቃኘ የመከላከልና የቁጥጥር ስልት መቀመር ያስፈልጋል፡፡ በእርግጥ አሁን ያለው ሁኔታ ሙሉ ለሙሉ ተስፋ የሚያስቆርጥ አይደለም፡፡ ለውጥ ሊመጣ የሚችልበት ዕድልም አለ፡፡ ይህን መልካም አጋጣሚ ለመልካም ሥርዓት ግንባታ ልናውለው ይገባል፡፡ ከትምህርቱ ጎን ለጎን ቁጥጥሩን በተሻለ መንገድ ማጠናከር አሻጋሪ ¾]' ውጤት ሊያስገኝ ይችላል፡፡

የፌዴራል መንግስትና የክልል መንግስታት የሥነምግባር ትምህርት ለማስፋፋት ጥረት እንደሚያደርጉ አውቃለሁ፡፡ በዚህ ረገድ ስለተገኘው ውጤት ግን በእርግጠኝነት የማውቀው ነገር የለም፡፡ አንድ መዘንጋት የሌለበት እውነት አለ፡፡ ለማስተማር የምንጥረው በንግግር ብቻ ከሆነ የትም አንደርስም፡፡ በተግባርና በቃል መካከል ብዙ ልዩነቶች አሉ፡፡ ሙስና በስውር የሚሠራ በመሆኑ ሙሰኞች በአደባባይ ንግግር እያሳመሩ በጓዳ ውስጥ ኢሥነምግባራዊ ተግባራቸውን ይፈጽማሉ፡፡ ሙስናን በአደባባይ ለማውገዝ የሙሰኛን ያህል ድምፅ ያለው ሰው የለም፡፡ አእምሮና ሕሊናው ለግብረገባዊና ሥነምግባዊ መርህ ተገዥ ካልሆነ ሰውን ስብከትና ትምህርት ብቻውን የፈለገውን ከማድረግ አያቆመውም፡፡ ለመርህ ተገዢ የሆነ ትውልድ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ «ማንም ቢያየኝም ባያየኝም ይህን ማድረግ የለብኝም፤ ምክንያቱም ተቀባይነት የሌለው ጎጂ ነገር ነው» ብሎ የሚያምን አእምሮ ያስፈልጋል፡፡ መልካም የሆነ ተግባር ለማከናወንም ማንንም የማይጠብቅ ሕሊና መፍጠር የሚያስችል ትምህርት ከሠጠንና ካዳበርን ለውጥ ይመጣል፡፡ በተለይ ታዳጊ ህፃናት እና ወጣቶች ላይ በትምህርት የሚዘራው ዘር እያደር ውስጣቸው እየበቀለ የራሳቸው ማንነት እየሆነ ይሄዳል፡፡ ስለዚህ የትምህርቱ ትኩረት በዚህ ዕድሜ ላይ ላሉት ወጣቶች ቢሆን ይመረጣል፡፡

በጉልምስና ዕድሜ ውስጥ ላሉ ዜጎች ይህንን ማስረፅ ትንሽ ይከብዳል፡፡ ስለዚህ ለዚህ ማሕበረሰብ የቁጥጥር ስልቱን በማጠናከር እና ትምህርትም ጎን ለጎን እየተሰጠ ቢሄድ ሁለቱም እየተደጋገፉ ውጤት ያስገኛሉ የሚል እምነት አለኝ፡፡ በሙስናና ብልሹ አሠራር ላይ የሚካሄደው ጦርነት ብልጭ-ድርግም የሚል ሳይሆን ያለቋረጥ የሚከናወን ሂደት መሆን አለበት፡፡ በአደባባይ ማውገዝና በግልፅ መቃወም፤ በሙሰኞች ላይም ጠበቅ ያለ ስልታዊ ቁጥጥር ማድረግ፤ ህብረተሰቡ እኩይ ባሕርያትንና ተግባራትን እንዲፀየፍ ያልቋረጠ ትምህርት መስጠት ትልቅ ለውጥ ያመጣል የሚል ተስፋ አለኝ፡፡

ሙስና ጉልበት አግኝቶ ሀገርን አሳሳቢ አደጋ ላይ መጣል የሚችለው የተበላሸ ፖለቲካዊና መንግስታዊ አስተዳደር ሲሰፍን ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ለሙስና መፈጠር ምክንያት የሚሆነው ሀገር የምትመራበት ሥርዓት እየነቀዘ ሲሄድ፤ ኢ-ዲሞክራሲያዊ አመራርና አሰራር ስር ሲሰድ፤ የህግ የበላይነት አቅም ሲያጣና ባለሥልጣኖች በሞራል ዝቅጠት ውስጥ ሲደፈቁ ነው፡፡ ሀገራችን ዛሬ በዚህ ሰው ሰራሽ በሽታ እየደማች ነው፡፡ ለ27 ዓመታት ኢትዮጵያን የገዛው የኢህአዴግ መንግሥት በሀገሪቱ ታሪክ ውስጥ ታይቶ በማያውቅ ፍጥነት በሙስና ወረርሽኝ አጠቃት፡፡ ሥርዓቱ ራሱ የፈጠረውን ሙስና እዋጋለሁ እያለ የተለያዩ እርምጃዎች የወሰደ ቢመስልም በለውጥ ኃይል ከአመራር እስከ ተገለለበት ጊዜ ድረስ ሙስናን ከመስፋፋት የገታው ነገር አልነበረም፡፡ በለውጡ ምክንያት ቢያደፍጥም ሙስና አሁንም በተለይ በታችኛው የሀገራችን የአስተዳደር እርከን ለውጡን በመገዳደር ላይ የሚገኝ መሆኑን መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡

ሙስና ሲጀምር በትንሹ ነው፡፡ ከዚያ በኋላ ግን ለመቋቋም የሚያስቸግር ይሆናል፡፡ በስውር የሚሠራና ውስብስብ ወንጀል በመሆኑም በቀላሉ ሊደረስበት አይችልም፡፡ ይህ ደግሞ ሙሰኞች በድርጊታቸው እንዲቀጥሉ ይገፋፋቸዋል፡፡ ለዚህ የሚመጥንና ህሊናን የሚገዛ ትምህርት ማዘጋጀትና በራሳቸው የሚተማመኑ ዜጎችን ማፍራት አማራጭ የሌለው ተግባር ነው፡፡ ይህ ሲሆን ህፃናትም ሆኑ አዋቂዎች የሙስናን አስከፊነትና መጥፎነት እየተገነዘቡ ይመጣሉ፡፡ ከዚሁ ጋር ሙስናን የመጠየፍ ባህል እያደገ ይመጣል፡፡ አንድ፤ ሁለት ሶስት ተቋማት በተናጠል በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ብቻ በሙስና ላይ የበላይነት ማግኘት አይቻልም፡፡ የፖለቲካ ሥርዓቱ ቁርጠኝነት እንዳለ ሆኖ ባሕርይንና አቅምን መሠረት ባደረገ ስልት ህዝቡን ከላይ እስከ ታች ማሳተፍ ያስፈልጋል፡፡ በተናጠል የሚደረጉ ጥረቶች የትም አያደርሱም፡፡

ሙስና እኮ ትልቅ ጠላት ነው፡፡ የሀገርን ቅስም ይሰብራል፡፡ የህዝብን የመደማመጥና የመተማመን ባሕል ያናጋል፡፡ ብርቱ የሆነ ፈተና ነው፡፡ ከውጪ የሚመጣ ሳይሆን በውስጣችን የተፈጠረ ጠላት ነው፡፡ ከውጭ ጠላት ይልቅ የውስጥ ጠላት አደገኛ ነው፡፡ አሳሳች መልክ አለው፡፡ ስለዚህ ትግሉ ቀላል አይሆንም፡፡ ሀገርን ከዚህ ግዙፍ ችግር ለመታደግ እጅግ ብዙ ነገር መሰራት አለበት፡፡ ቀደም ሲል እንደ ተጠቀሰው የምንፈልገውን ለውጥ ለማምጣት በተቀናጀና በተናበበ መንገድ ብዙሃኑን ያሳተፈ የተራዘመ ጥረት ማድረግ አለብን፡፡ ግለሰቦች በራስ ተነሳሽነት በራስ ላይ እርምጃ በመውሰድ ከሙስና መፅዳት ይችላሉ፡፡ በዚህ ተግባር ውስጥ የተዘፈቁ የቅርብ ሰዎች ላይ ሳይቀር ትግል ማድረግ የግድ ይላል፡፡ የአስተሳሰብ ለውጥ ለማምጣት የሚጠይቀው ድካምና የሚያስከፍለው ዋጋ ቀላል አይደለም፡፡ የአስተሳሰብ ሥርዓትን ዘወትር እያጠኑ ቀዳዳ እንዳይከፈት እርምጃ መውሰድ አስፈላጊ ነው፡፡ ባጭሩ ሙስናን ለመታገልና ለማቆም ጠንካራ ትምህርት ከመስጠት ጎን ለጎን መደረግ ያለባቸው ሌሎች ተጓዳኝ ነገሮች አሉ፡፡ በእኔ አስተሳሰብ ሙስና ለዚህ ትውልድ ትልቁ አደጋ ነው፡፡ ባሉብን በርካታ የሥነምግባር ህመሞች ላይ ሙስና ተጨምሮ በብርቱ ካቆሰለን መልሶ ለማገገም በእጅጉ ይከብደናል፡፡

ፀረ-ሙስና፡- በሀገራችን በብዛት የሚታዩት የሥነ ምግባር ጉድለቶች ቢዘረዝሩልን

ዶ/ር ጠና፡- በጣም በርካታ ችግሮችን መዘርዘር እንችላለን፡፡ ለምሳሌ መዋሸት በእጅጉ ተስፋፍቷል፡፡ በአደባባይ የምንናገረውን በተግባር ካለመፈፀም ጀምሮ በውሸት ሕዝብን ማደናገር እየበዛ ነው፡፡ በንግግራችን ውስጥ፣ በስልክ ልውውጥ ወቅት፤ በመረጃ ልውውጥና በዘገባ አቀራረብ ውስጥ ውሸትን በስፋት እናገኛለን፡፡ ሙስናን ተመልከት - ሌላ የሥነ-ምግባር ጉድለት ነው፡፡ ድሮ ጉቦ በመባል በስውር ገንዘብ ይሰጥ ነበር ወይም በዓይነት የሆነ ነገር ይሰጥ ነበር፡፡ ዛሬ ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ በድርድር እንደሚተላለፍ ይሰማል፡፡ ምንና የት እንደሚሰራ የማናውቀው ሰው በአጭር ጊዜ ውስጥ የበርካታ ሰማይ ጠቀስ ፎቆች ባለቤት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ይሄ ነው የሚባል ወይም በሕግ የሚታወቅ ሥራና ገቢ የሌለው ግለሰብ የበርካታ ካሚዮኖች፣ የትላልቅ እንዱስትሪዎችና ሆቴሎች ባለቤት ሆኖ ልታገኘው ትችላለህ፡፡ ይህ ታዲያ ተለፍቶበት ወይም ተደክሞበት ያልተገኘ ሀብት ከሙስና በቀር በምን ተአምር ይገኛል? እነዚህ ሁሉ በቅርብ ያየናቸውና የምናውቃቸው ታሪኮች ናቸው፡፡ ሌላው ክህደት ነው፡፡ ውልንና እምነትን በመጣስ፤ ቃልኪዳንን በማፍረስና በመሳሰሉት መንገዶች ክህደት የሚፈጽሙ ወገኖች በዝተዋል፡፡ በዚህ ምክንያት የመተማመን ባሕላችን እየተዳከመ ነው፡፡ አሁን አሁን ስርቆትን እንደሥራ የሚቆጥሩ ዜጎች፣ ቅንነት የጎደለው አገልግሎት የሚሰጡ፤ ምርትን ከባዕድ ነገሮች ጋር ቀላቅለው ለአገልግሎት የሚቀርቡ፤ ምዝበራን ሳይሣቀቁ የሚፈፅሙ ሰዎች ቁጥር እየበዛ መጥቶአል፡፡ በዚህ መልክ ብዙ የሥነ ምግባር ጥሰቶችን መዘርዘር ይቻላል፡፡

ፀረ-ሙስና፡- ተቀባይነት ያለው ሥነምግባርን በሀገር ደረጃ ለማስፈን ከማን ምን ይጠበቃል?

ዶ/ር ጠና፡- በሀገር ደረጃ ከላይ ለሥነምግባር ችግር ማስፋፋት ኃላፊነት አለባቸው ያልኳቸው አካላት በሙሉ መልካም ሥነምግባር ያለው ዜጋን በማፍራት ረገድ ብዙ መሥራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ግለሰብ፤ ቤተሠብ፣ ህበረተሰብ፣ ትምህርት ቤቶች፣ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት፤ የፖለቲካና የሀይማኖት ድርጅቶች ሁሉ ትውልዱን በተሻለ ሁኔታ ቀርፆ መልካም ዜጎችንና ሰናይ ማሕበረሰብን ለመፍጠር ከፍተኛ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ሁላችንም ያገባናል፡፡ መልካም ሥነምግባር ያለው ልጅ እንዲኖረው የማይፈልግ ቤተሰብ፣ መልካም ዜጋ እንዲኖረው የማይሻ መንግስትና ሀገር የለም፡፡ ምላሽ ማግኘት የሚኖርበት ጥያቄ ግን ይኸን ማሳካት የሚቻለው እንዴት ነው የሚለው ነው፡፡ ለዚህ ቁጭ ብለን መመካከር ይኖርብናል፡፡ የጋራ አቋም ይዘን ወደ ተግባር መግባትም ይጠበቅብናል፡፡

ተግባራችንን ቅርባችን ካለው ነገር መጀመሩ ተመራጭ ነው፡፡ ከራሳችንና ከቤታችን መጀመር አለብን፡፡ ለእያንዳንዱ ሰው ከራሱ በላይ የሚቀርበው ነገር የለም፡፡ ለኔ ከኔ በላይ የሚቀርበኝ ነገር የለም፡፡ ስለዚህ ሙስናን ለመዋጋት ከራሴ መጀመር አለብኝ፡፡ #ሙስናን ለመስራት የሚያስብ አእምሮ፤ ሙስናን ለመፈጸም የሚንቀሳቀስ እጅ ሊኖረኝ አይገባምም$ ብዬ ለራሴ ቃል መግባት አለብኝ፡፡ ይህን ቃል የትም ይሁን የት ማክበርና መተግባር አለብኝ፡፡ የሌሎችን ኢሥነምግባራዊ ተግባር መኮነን የምችለው በመጀመሪያ ለራሴ ሙስናን መጠየፍ የሚያስችል አቅም ካገኘሁ ነው፡፡ የሀገራችን ስጋት ዋና ምንጭ ለኔ የውጪ ጠላት ሳይሆን የውስጥ እንከኖቻችን ናቸው፡፡ መፍትሄውም ከዚሁ ከውስጣችን የሚገኝ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝቦች ልማዳዊ ክህሎቶች፤ ዕውቀቶችና እሴቶች በአብዛኛው ተቀራራቢ ናቸው፡፡ የቋንቋ ካልሆነ በስተቀር ብዙ የተራራቁ የሥነምግባር እሴቶች የሉንም፡፡ አንዱ ጋር ያለውን ጥሩ ነገር በሌላው ዘንድ ካለው ጋር በማጣመር የተሻለ ነገር መሥራት ይቻላል፡፡ ክርስቲያናዊ ይሁን እስላማዊ፤ ሰማያዊም ይሁን ምድራዊ፤ ልማዳዊ ይሁን ዘመናዊ የግብረገብ እሴቶችን ወስደን ለሀገራችን በሚበጅና ለሁላችን በሚጠቅም መልኩ ማዘጋጀት እንችላለን፡፡ ይህ በዘመናዊ ዕውቀት መታገዝ ይኖርበታል፡፡ ይህ ሕዝባችንን ይበልጥ ያስተሳስራል፡፡ በትንንሽ ልዩነቶች ትልቁን አንድነታችን መናድ አይኖርብንም፡፡ መተባበርና እርስ በእርስ መከባበር አለብን፡፡ ከእርሱም የሚጠቅመንን በመውሰድ ማንንም የማያገል፣ ማንንም የማያስቆጣ፤ ይልቁንም ለሁሉም የሚበጅና ሀገራችንን ወደፊት የሚያራምድ ሥነምግባር የተላበሰ ትውልድ ለመቅረፅ የሚያስችል አቅም መፍጠርና ዝግጅት ማድረግ እንችላለን፡፡

ሶሻሊዝም ብለን የምሥራቁን ዓለም ደጅ ሥንጠና ነበር፡፡ ዲሞክራሲ ብለን የምዕራባውያንን አስተሣሰብ ስንለምን ቆይተናል፡፡ እስካሁን ከሁለቱም ከትርምስና ከመስዋዕትነት የዘለለ ጥቅም አላገኘንም፡፡ የቀረን አማራጭ ወደ ራስ መመለስ ነው፡፡ እዚህና እዚያ እያልን ህዝባችንን ማደናገሩን ትተን ለእኛ አፈር፣ ለሀገራችንና ለሕዝባችን የሚስማማውን መልካም ነገር ከራሳችን እሴትና ትውፊት ማመንጨት አለብን፡፡ አሁን ከምዕባራውያን ለመኮረጅ የምንጥረው ዲሞክራሲ እነርሱ አዘመኑት እንጂ ምንጬ እኮ እኛ ነበር፡፡ ለህዝባችን ቅርብ የሆነውን ሀገራዊ ፍልስፍና፤ አስተሳሰብና አመለካከት በማዘመን ብናቀርብለት በቀላሉ የራሱ ያደርገዋል የሚል እምነት አለኝ፡፡ ከሀገራችን የተገኘውን ዕውቀትና ክህሎት፤ እምነትና ጥበብ አዳብረንና አዘምነን ከራሳችን ህይወትና ልማት ማዛመድ አይከብደንም፡፡

ምንም የሌለን ህዝቦች አይደለንም፤ የኛ የሆኑ በጊዜ ብዛት እየደበዘዙ የሄድ በርካታ እሴቶች የነበሩን ህዝቦች ነን፡፡ የራሳችን አመለካከቶች እምነቶች፣ አስተሣሠቦችና ፍልስፉናዎች አሉን፡፡ እነዚህን ለእኛ በሚስማሙን መልክ በማዘመን ልጆቻችንን በባእድ አስተሣሠብ ሣይሆን በራሳችን ፍልስፍናና ሥነልቦና በተቃኘ አመለካከት እናሳድጋለን፡፡ ሊጠቅሙን የሚችሉ ዓለም የፈጠረቻቸውን ዕውቀቶችና እሴቶች ሳንዘነጋ ማለቴ ነው፡፡ ዓለምን በራሳቸው መነፅር የሚመለከቱ፣ በራሳቸው ሚዛን የሚለኩ፤ በራሳቸው የሚተማመኑና ጠቃሚና ምክንያታዊ የሆኑ እሴቶችን የሚያከብሩ ዜጎች እንፈጥራለን፡፡ ይህ ግን ቀላል አይደለም፡፡ ለዚህ የሁላችንም ቁርጠኝነት ያስፈልጋል፡፡ በጉዳዩ ላይ አምነን ሁሉንም ነገር ኢንቨስት ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡ የሚያሸጋግሩ ሥራዎችን እየሠራንና የጋራ መግባባት እየፈጠርን ከሄድን የማንሻገረው ችግር አይኖርም፡፡ ስለዚህ ሀገርን እንደገና ለመሥራት ትውልድን በሥነምግባር ማነፅን ዋነኛ ተግባራችን አድርገን መንቀሳቀስ አለብን፡፡ መልካም ነገር ከሰራን ፈጣሪ ከጎናችን ይሆናል፡፡

# ኪነ-ጥበብ

## እንዲህ ነው ዘመኑ፤

ጉስቁልቁል...ቁልቁል ያለ ነው፤ መናኛ ነው ልብሱ፣
ጉቦን ይጠየፋል፤ ፍትሕ፣ ርትዕ ነው ምሱ፤
ከውኃ ጥርት ያለች፣ የፀዳች ናት ነፍሱ፤
እሳት የሚተፋ፣ እሳት ነው ምላሱ፤
ለሕዝቦች የቆመ፣ ለሕዝብ የሚሠራ፣
ለሕዝብም የሚሞት፣ ሕዝብ ነው ትራሱ።
‹‹ማን?›› አትሉም?
ሕዝብ--- ማን?
እሱ፤
እንዲህ ይነገራል፤ እንዲያ ይናገራል ሰውየው ስለእሱ።
ሰውየው...!
በትልቅ አዳራሽ፣ የትልቅ አገር ሕዝብ በአንድነት ሰብስቦ፣
‹‹እህ...ህ..ም!›› አለና የተዘጋ ድምጹን በህምህምታው አጥቦ፣
‹‹ታዲያስ?›› ሲል ጀመረ የስብሰባ ግብሩን በኩራት ተጠብቦ።
ይህንን ስሰማ ገጠር የሚኖረው ወንድሜ ትዝ አለኝ፤
እንዲህ ያጫወተኝ፤
ትዝብቱን፣ ስጋቱን በፍርሃት ያወጋኝ፤
‹‹አንዱን ዘበናይ ሰው...
እንደምን ዋልህ? ብለው ‹እንደምን ነህ?› አለኝ፤
እግዚአብሔር ይመስገን ሊቀር ነው መሰለኝ››
ያለኝ... ትዝብቱ ትዝ አለኝ።
ሰውየው ቀጠለ፤
‹‹ዛሬ እምንወያይ...
መልካም አስተዳደር እንደ እህል ተዘርቶ ባገር ካልበቀለ፣
ኪራይ ሰብሳቢነት አደጋ መሆኑ እማይቀር ነው!›› አለ፤
ቀጠለ...፤
‹‹ላይላዩን ሲያዩዋቸው ደጋግ የሚመስሉ፣
ኪራይ ሰብሳቢዎች ከውስጣችሁ አሉ›› ፎለለ።
ከተሰብሳቢው ውስጥ በጣም የቆዘሙ፣
ፈቃድ ሳይጠይቁ፣ እጅ ሳያወጡ አንድ አዛውንት ቆሙ፤
‹‹ሦስት መቶ እሚከራይ አንድ ክፍል ቤት አለኝ፤
ገብቶኛል፤ በእሱ ነው ‹ክራይ ሰብሳቢ› እያልህ እንዲህ
የምትዘልፈኝ፤
ገብቶኛል፤ መች ጠፋኝ?
እኔ የስበር ልጅ! ከዚህ እንደወጣሁ፣
ያን ምስኪን ተከራይ አንገቱን አንቄ አስወጣልሃለሁ››
ብለው ሲቀመጡ፣
ብዙ ውሪ ድምጾች እንደ ተቆላ ኑግ ባንድነት ተንጣጡ።
‹‹እዚህ ጋ! እዚያ ጋ!››
ብዙ ድምጽ ተሰማ፤ ብዙ እጅ ተዘረጋ፤
ሰውየው ናወዘ፤ በስሜት ተላጋ፤
‹‹ዝም በል! የሰው መንጋ!››
ብሎ ሕዝቡን ሰድቦ ስብስባውን ዘጋ።
በዚህ ብቻ ሳያርፍ፣
ሌላም ቀን አየሁት ሕዝብን እንዲህ ሲዘልፍ፤
በድፍረት ሲወርፍ።
‹‹ማ...ን?›› አትሉም?
እሱ ነዋ ጀግናው የሁላችንም አፍ።
ለእኛ ‹‹እየታገለ›› እኛኑ መልሶ በምላሱ እሚገርፍ፤
በምላሱ ሳንጃ ቆዳህን የሚገፍ።
አንዲት ምሽት ላይ፣ አንዲት ደግ ምሽት፣
ከቤቴ ቁጭ ብዬ ቴሌቪዥን ስከፍት፣
እንዳልሆነ ሆኖ ያንን ሰው አየሁት።
እንደ ጥጃ ታስሮ፣ በፖሊስ ሠራዊት እንደ በግ ሲነዳ፣
አየሁት ያንን ሰው ተከርችሌ ጓዳ።
‹‹ማ...ን?›› አትሉም?
ሰውየውን ነዋ! ያንን ያገር አላል፤ ያንን ያገር ዕዳ።
ደ..ሞ ሌላ...!
መስቀል ተሸክሞ በእምነት አደባባይ የተንጎማለለ፣
‹‹ጌታን!...ማርያምን! ወዘተን!...›› እያለ፣
ደጋግሞ እየማለ፤
‹‹ስራብ አበላኸኝ? ስጠማ አጠጣኸኝ?›› የሚለውን ትእዛዝ
ከማቴዎስ ወንጌል እየመነዘረ፣
‹‹ያለው ለሌለው ይስጥ!›› ብሎ በዓውደ ምህረት ደፍሮ
እያስተማረ፣
ብሎ እየመከረ፤
‹‹ወቼ ጉ..ድ!›› ተብሎለት ተከብሮ እንዳልኖረ፣
‹‹አታመንዝር!›› ብሎ ጮኾ እንዳልነገረ፤
‹‹አትስረቅ!›› እያለ ሲለፍፍ እንዳልኖረ፤
ሙዳዬ ምፅዋቱን ሲገለብጥ ታይቶ ትናንት ታሰረ።
‹‹ማ...ን?›› አትሉም?
ሰባኪው!
በጩኸቱ ብዛት አገር ምድር አዋኪው፤
ከጸሎት ቤት ቆሞ በፈጣሪው ፈንታ ወርቅ ብር አምላኪው።
ደ..ሞ! ደ..ሞ ሌላ!
አገር የሚያደንቃት፣
በውበቷ ብዛት ሁሉ እሚፈዝላት፤
አለች አንዲት ሸጋ፣ ልቅም ያለች ቆንጆ፤
ለትዳሯ ታማኝ፣ ለሠራቸው ጎጆ፤
ሆኖም...!
ለባሏ ያላትን ክብር ስታስቀድም፣
ሴቶች ባሏን ሲያዩ፣ ሲያናግሩ አትወድም፤
ከባሏ ክንድ ላይ፣ ከጎኑ ተኝታ ጀርባውን ታያለች፤
አንሶላ፣ ትራሱን፣ ብርድ ልብሱን ሁሉ ትጠርጥራለች፤
አንድ ቀን...
ያውም በባሏ አልጋ ከዘበኛዋ ጋር ተኝታ ተገኘች።
‹‹ማ...ን?›› አትሉም?
እሷ ናታ!
በዚያ ምስኪን ባሏ ለትዳሯ ቀንታ።
ሌ..ላም አለ፤
አንድ ቀን በድንገት ደረቴን ታምሜ፣
አቅራቢያዬ ካለ ሆስፒታል አዝግሜ፣
ተመረመርሁና፣ ተበረበርሁና፣
ላገኝ የድሮውን የተሟላ ጤና፤
‹‹እ...እ.. ዌል!
ምንም ማለት አይደል፤
ብቻ ሲጋራ አቁም፤
በቃ ጫት አትቃም!
ቢኬርፉል ማይዲር!
መጠጥ እንዳትቀምስ›› ሲለኝ፤
ውኃስ?
የእኔው መልስ።
እንዳልሰማ መስሎ፣ ከወረቀቱ ላይ ትንሽ ነገር ጫረ፤
ወዲያው ወደ ሌላው በሽተኛው ዞረ።
የዚያን ለታ ምሽት...
በአንድ እጁ መለኪያ፣ በሌላው ሲጋራ፣
ጨብጦ ሲጃጃል፣ ወረፋ አልቦ ተረት ሲተርት፣ ሲያወራ፣
አላገኘሁትም ከትሁኔ ጠጅ ቤት ከቲፕሲዎች ጎራ?
‹‹ማ...ን?›› አትሉም?
ሐኪሙ ተዘራ፤
ግን...! ግን...
ይህ በመሆኑ፣ ምንም አትዘኑ፤
ይልቅ የሙሰኞች እንዳይሆን ዘመኑ፤
ባለሸጋ ምግባር፣ ምስጉን ዜጎች ሁኑ፤
አገር አውዳሚውን፣ ትውልድ ገደዳዩን ሙስናን ኮንኑ፤
ከሙስና ደዌ አገርን ፈውሱ፣ ትውልድን አድኑ!

(በአበረ አዳሙ ጥር 28/1998 አዲስ አበባ)

# መልካም ዜጋ

## ሥነምግባራዊ አመራርና ሙስና መከላከል

ሥነምግባር የተለያዩ ሀገራት እንደ ባህልና እሴታቸው የተለያየ ትርጉምና ፍች የሚሰጡት ቢሆንም ጠቅለል ሲል በአንድ ህብረተሰብ የጋራ ሕይወት ተቀባይነት ያለውንና የሌለውን፣ ጥሩውንና መጥፎውን ለመለየት፣ ለመግለጽና ሥርዓት ለማስያዝ የሚረዳ እንዲሁም የሙያና የሞራል ግዴታዎችን ለመወጣት የሚያስችል ልኬት ነው፡፡

በሌላ በኩል ሥነምግባር ከማህበረሰብ እውነታዎችና እሴቶች በመነሳት ትክክለኛና የተሳሳተ፣ ጥሩና መጥፎ የሚባሉ ነገሮችን እና ባህሪያትን በመደባቸው ለይቶ የማስቀመጥ እና ከዚህም ተሻግሮ በድርጊት የመግለጽን ማለትም ከመጥፎ ነገሮች ተቆጥቦ የጥሩ አስተሳሰቦችና ተግባራት ባለቤት ሆኖ መገኘትን የሚያመላክት፤ ከህጋዊ አስገዳጅ ሁኔታዎች በዘለለ የሰዎችን ሚዛናዊና ምክኒያታዊ አስተሳሰብና ከዚህም በመነጨ ሊፈጠር የሚችልን የህሊና እርካታ ወይም ተጠያቂነትን መሰረት የሚያደርግ አንጻራዊነት ያለዉ የባህሪ/ስብእና መገለጫ ሆኖ ይታያል፡፡ ከዚህ አጠቃላይ ትርጓሜ በመነሳት ከሙስና ጋር ያለዉን ቀጥተኛ ተዛምዶ ለማየት እንችላለን፡፡



ሙስና ዓለም አቀፋዊ ይዘት ያለው ችግር የመሆኑን ያህል የቃሉ ጽንሰ ሀሳባዊ ፍቺ ወይም ምንነቱ የሚገለጽበት መንገድና ትንታኔ በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ያለው አንድ ወጥ ትርጉም የለዉም፡፡ ሙስና እንደየሀገሩ ባህልና የአኗኗር ዘይቤ፣ ከሚያደርሰው የጉዳት መጠን፣ ከሚፈጸምበት መንገድ፣ ከተግባሩ ዓይነትና ከፈፃሚዎቹ አንጻር የተለያዩ ትርጓሜዎች ይሰጠዋል፡፡

የተባበሩት መንግስታትና የአፍሪካ ህብረት የፀረ-ሙስና ስምምነትም ሙስናን አንድ ወጥ ትርጉም ከመስጠት ይልቅ የተለያዩ መገለጫዎችን በዝርዝር ያስቀምጣሉ፡፡ ያም ሆኖ በጥቅሉ ሲታይ ሙስና ከህዝብ የተገኘን ሥልጣን ወይም ኃላፊነት ለግል ጥቅም ማዋል ሌላውን ወገን ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት ሲባል ሥልጣንና ኃላፊነትን ያለአግባብ መገልገል ሲሆን ዋነኛ መንስዔውንም በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡

የመጀመሪያው ምቹ ሁኔታ/Opportunity/ ሲሆን ይህ በህግ ወይም በስርዓት ውስጥ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል፣ ለማጋለጥና ለማረም የሚያስችል ውጤታማ ስርአት አለመዘርጋትን የሚያመላክት ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ የሚገለጸው አበረታች ሁኔታ/Motivational factore/ የሚባለው ነው፡፡ አበረታች የሙስና መንስኤ ከሰዋዊ ምክንያቶች የሚመነጭ ሆኖ ለችግሩ መከሰት ወይም መባባስ አይነተኛና ቀዳሚ ምክንያት ተደርጎ የሚወሰድ ነዉ፡፡ በዚህ ዙሪያ ስግብግብነት፣ ላልተገባ ጥቅም መማለል፣ ሰበበኝነት፣ ጽናት ማጣት፣ ተገቢ ያልሆነ ምክንያት በመፈለግ የጥፋተኝነት ስሜትን ላለመቀበል የሚደረግ የተሳሳተ አመክንዮ/ከራስ ለመደበቅ መሞከር/ ወዘተ ተጠቃሾች ናቸዉ፡፡ እነዚህ ጉዳዮች በዋናነት የችግሩ አይነተኛ ምንጮች ከመሆናቸው ባሻገር ከሥነ-ምግባር ብቃት ወይም ደካማነት ጋር ቀጥተኛ ቁርኝት እንዳላቸዉ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

የሰው ልጅ ከተፈጥሮ ህግጋት ባሻገር መለኮታዊና ሰብአዊ ህጎችን መሰረት አድርጎ በእነዚህ ህግጋቶች መተዳደርና መዳኘት ከጀመረ ጀምሮ ማህበረሰቡን ከተሳሳቱ ድርጊቶች ሊቆጥቡና ከጥፋት ሊታደጉ ይችላሉ የሚላቸውን በርካታ ስርአቶችን እየዘረጋ፣ እቀባዎችን እየጣለ፣ ድንጋጌዎችን እያስቀመጠና እያሻሻለ አሁን እስከምንገኝበት ዘመን ደርሷል፡፡ እነዚህ ህግጋቶች ምንም እንኳን መልካሙን ነገር ከመጥፎው ለመለየትና ልቅ የሆኑ ልማድና አስተሳሰቦችን ለማስተካከል ወይም ለማረቅ ያላቸው አስተዋጽኦ የጎላ መሆኑ ባይካድም ጥፋትና ጥፋተኞች፣ ወንጀልና ወንጀለኞች፣ ኢ-ሥነ-ምግባራዊ ተግባራትና ፈጻሚዎቻቸው ከመደብዘዝ ይልቅ የማህበረሰቡን የዕድገት ደረጃ ተከትለው እየተራቀቁ፣ እየሰፉና ባህሪያቸውን እየለዋወጡ እንደመጡ ለመገንዘብ አዳጋች አይሆንም፡፡

ጥንታዊው የሃሙራቢ ህግ ለዚህ ሁነኛ ማሳያ ሆኖ መቅረብ የሚችል ይሆናል፡፡

የባቢሎን ንጉስ የነበረው ሃሙራቢ ከግንባታ ስራዎች ሥነምግባር ጋር በተያያዘ በ 1758 BC ባዎጣው ድንጋጌ መሰረት አንድ ተቋራጭ የገነባው ቤት ፈርሶ ባለቤቱን ከገደለ እራሱ መገደል አለበት፤ የባለቤቱን ሚስት ወይም ልጅ ወይም ሌላ የቅርብ ሰው ከገደለም በተመሳሳይ መልኩ ተመሳሳይ ቅርበትና ዝምድና ያለው የተቋራጩ ወገን መገደል ያለበት መሆኑን እና የተጠናቀቀው ወይም በመሰራት ላይ ያለው ግንባታ ጉዳት ከደረሰበት ወይም የጥራት ችግር ካለበት ደግሞ በተቋራጩ ወጪ እንደገና ከመገንባት ጀምሮ ተመጣጣኝ ካሳ መካስ ያለበት መሆኑን ይደነግጋል፡፡ ይሁንና እነዚህና መሰል ጠንካራ ህጎች ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ቢኖሩም፤ ከዚያም ወዲህ ጠንካራ ህግ አስፈጻሚ ተቋማትና ድንጋጌዎች ቢፈጠሩም ሁኔታዎችን በሚፈለገው ደረጃ መቀየር አልቻሉም፡፡ ይልቁንም በሥነምግባር ጉድለትና ስግብግብነት የሚፈፀሙ የሙስና ችግሮች አሁንም ድረስ ፀባያቸውን በየጊዜው እየቀያየሩ በሰፊው የዘመናችን የዕድገት ፈተና ሆነው እንደቀጠሉ ናቸው፡፡

ሙስና እንደ አንድ በዓለማችን የተደቀነ ጉልህ ማህበራዊ ችግር ወይም ክስተት በራሱ የሚያስከትለው ጉዳት እንደተጠበቀ ሆኖ ከሌሎችም የሰው ልጅ የህልውና ጠንቅ ከሆኑ ወንጀሎች ጋር ማለትም በአካባቢ ብክለትና ውድመት፣ በህገ-ወጥ የጦር መሳሪያ፣ መድሃኒቶች፣ የሰዎች ዝውውር፣ እጽ እና ገንዘብ ዝውውር እንዲሁም ሽብርተኝነት እና የህጻናት ጉልበት ብዝበዛ፣ በመሳሰሉ ዓለም አቀፍ ወንጀሎች ጀርባ እንደ ጥላ የሚከተልና በተለይም ደግሞ የዜጎች የመጨረሻ ዋስትና እንደሆነ በሚነገርለት የፍትህ ስርዓት ውስጥ የፍትህን አቅም በማሳጣት ዜጎችን ለተስፋ ቢስነት በመዳረግ የሰላምና መረጋጋት ጠንቅ በመሆን ላይ ያለ ወንጀል ነዉ፡፡

ከዚህ አንጻር ችግሩን ለመፍታት በርካታ ዓለም አቀፋዊ፣ አህጉራዊና ሃገራዊ ህግጋትና ድንጋጌዎች ወጥተዋል በመተግበርም ላይ ናቸዉ፡፡ ምንም እንኳን እነዚህ ማህበረሰባዊ እቀባዎችና ህጋዊና ልዩ ልዩ የተጠያቂነት ሥርአቶች ሙስናና ኢ-ሥነምግባራዊ ድርጊቶችን ለመከላከልና እንዲቀንሱ ለማድረግ ያላቸው አስተዋጽኦ ባይካድም ከሰዎች ህሊናዊና ሞራላዊ ጥንካሬ በመነጨ በመልካም ሥነ-ምግባር የታነፀ ግለሰብ፣ ቤተሰብ፣ ማህበረሰብና ማህበራዊ ግንኙነት የሰፈነበት አካባቢ መፍጠር እስካልተቻለ በዚህ ዙሪያ ሊፈጠሩ የሚችሉ ችግሮችን ከመቅረፍ አኳያ አስተማማኝ ዋስትና ሊሆን አይችልም፡፡

ለዚህም ነው መልካም ሰዎች በመጥፎ የህግ አስተዳደርና ስርዓት ውስጥ መልካም ሆነው መልካም የሚባሉ ተግባራትን ሲያከናውኑ የሥነምግባር ጉድለት ያለባቸውና ስግብግብ ሰዎች ደግሞ በጥሩና አመቺ ህግና ስርዓት ውስጥ ለመጥፎ ሃሳባቸው ማስፈጸሚያ የሚሆኑ ቀዳዳዎችን በማፈላለግና በመሰርሰር ተጠምደው ይውላሉ የሚባለው፡፡

በመሆኑም በአሰራር ውስጥ የጥፋት እድሎችን የማጥበብና በተፈጠሩ ችግሮች ላይ የእርምት እርምጃዎችን ተፈጻሚ ማድረግ እንደተጠበቀ ሆኖ በግብረገብና ሥነምግባር ግንባታ በትኩረት መስራትና መልካም ዜጋን መገንባት የበለጠ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ የችግሩ ሁነኛ ቁልፍ መፍትሄ ነው፡፡

የሀገር መሪዎች ባላቸው ስልጣንና ኃላፊነት በሃብት ላይ ይወስናሉ ያስተዳድራሉ፤ ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎችን በአስተሳሰብና በመልካም ምግባር የመቅረጽ እድል አላቸዉ፤ እንደ ሀገር የሚከሰቱና ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን የማረም ኃላፊነትና ስልጣን ተሰጥቷቸዋል፤ ስርዓትም ይዘረጋሉ፤ ይህ የሚሆነውና ሙስናን መከላከል የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት የሚችሉት ደግሞ በመልካም ሥነምግባር የታነጹ እስከሆኑ ድረስ ብቻ ነው፡፡ የሙስና መከላከልና የሥነምግባራዊ አመራር ተዛምዶ ወይም ግንኙነት የሚመነጨውም ከዚህ አንፃር ይሆናል፡፡

የተቋማት ቁመና በዋነኛነት በመሪዎቻቸው ሥብዕና የሚወሰንና የመሪዎቻቸው የመስታወት ግልባጭ/ነጸብራቅ/ እንደመሆኑ፤ የተቋማዊ ባህል/ ሥነምግባር/ ግንባታ ጉዳይም የበላይ አመራሩ / የፖለቲካ፣ የቢሮክራሲ፣ የእምነት ተቋማት.../ የተለየ የትኩረት ጉዳይ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ይህም የሥነምግባራዊ አመራር (Ethical Leadership) ጉዳይን ቀጣይነት ያለው የተቋማዊ ባህልና እንቅስቃሴ ምሶሶ ያደርገዋል፡፡

ሥነምግባራዊ አመራር ስንል የመሪዎችን በግል ስብእናቸው መልካም የሚባሉ ባህሪያትን ተላብሰው ከዚሁ ባህሪያቸው የሚመነጩ ድርጊቶችን የመከወን ብቃት ከማመላከት ባሻገር በዙሪያቸው ወይም በሥራ አካባቢያቸው ያሉ ተከታዮቻቸው ዘንድም አወንታዊ የሆነ ተጽእኖ በመፍጠር ወደዚህ አይነቱ ባህሪና ተግባር እንዲሳቡ ማድረግ መቻልን የሚያካትት ተግባር ነው፡፡

ስለሆነም መሪዎች ለሌሎች ሰዎች የመልካም ነገር ተምሳሌት የመሆን፣ ሌሎችንም የጉዳዩ አቀንቃኝ አድርጎ የማሰለፍ፣ ሁሉንም አካታች መለኪያዎችን የማስቀመጥና ከዚህ አንፃር አካባቢያቸውን የመመዘን፣ የማረምና የማትጋት እንዲሁም በውሳኔ አሰጣጣቸወ የበቁ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡

በየደረጃው ያሉ አመራሮች ለሚገኙበት የአመራር ቦታ የሚመጥን ብቃትና ስልጣን ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ይህ ብቃት አልሚ ሆኖ ሲተገበር የሚጠቅመውን ያክል በተቃራኒው ጎጂ ሆኖ ሲመነጭና ወደ ተግባር ሲለወጥ ደግሞ ጥፋቱ የከፋ ይሆናል፡፡ የአንድ ተቋም የሥነምግባር ሁኔታ በዋናነት ከመሪዎች ጋር የሚተሳሰረውም ከዚህ አንፃር ነው፡፡ ይህ ብቃትና ስልጣን ውሳኔዎችን ለመወሰንና ለማስፈፀም ከሌላው በተለየ በእጃቸው የሚጨብጡት ቁልፍ መሳሪያ ነው፡፡ በመሆኑም ከግለሰባዊ እርካታቸው በዘለለ የማህበረሰቡን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ ሥነምግባራዊ ድርጊቶችን በመፈፀም ስኬትን ማእከል ያደረጉ ሊሆኑ፤ አለያም በተቀራኒው የኢ-ሥነምግባራዊ ድርጊቶች መሪ ተዋናይ ሆነው ሊሰለፉና ጥፋትን ሊያመርቱበት ይችላሉ፡፡

በመሆኑም በየደረጃው ለሚገኙበት የውሳኔ ሰጭነት ተግባር የሚመጥን ማንነት፣ የኃላፊነት ስሜትና ሞራላዊ ብቃት እያዳበሩ መሄድ ይጠበቅባቸዋል፡፡ “ሌሎችን መግዛት ጥንካሬ ነው፤ ራስን መግዛት ግን እውነተኛ ሃይል ነው”፡፡ እንደሚባለው፡፡

መልካም ሥነምግባር የተላበሱ መሪዎች(Ethical Leaders) የሚይዟቸው የተለያዩ መርሆዎች ወይም ባህሪና መገለጫዎች ያሉ ሲሆን የሚከተሉት በስፋት ይገለጻሉ፡፡ በድርጊታቸው አርአያ ሆኖ መታየት የሚጠበቅባቸዉ እንደመሆኑ ሁሌም ከአድሏዊነትና ኢፍታሃዊ አሰራር የተቆጠቡ፣ ለሰዎች ትልቅ ክብር የሚሰጡ፣ እምነት የሚጣልባቸው ከመሆናቸው ባሻገር እነሱም በዙሪያቸው ባሉ ሰዎች ላይ እምነትን የሚያሳድሩ፣ እራስ ወዳድ ያልሆኑና የተከታዮችን ገዥ ፍላጎት የሚያስቀድሙ፣ በተቋማት ውስጥ የጋራ እሴትና አስተሳሰብ በመፍጠር ላይ

## መልካም ዜጋ

የሚያተኩሩ፣ ሁሌም ቢሆን የሚወስኗቸው ውሳኔዎች ከተቋሙ አጠቃላይ ግቦችና እሴቶች ጋር የተገናዘቡ መሆናቸውን የሚያረጋግጡ፣ ትክክለኛ ውሳኔዎችን በትክክለኛ ጊዜ በትክክለኛ ምክንያት ላይ ተመስርተው የሚፈፅሙ ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሥነምግባራዊ ምህዳሩ ላይ /ethical ecology/ ተጽዕኖ የሚፈጥሩ ማህበራዊና ተቋማዊ ሁኔታዎች ውስጥ የሚገኙ እንደመሆናቸው ሁኔታዎችን በአግባቡ የመረዳትና የመተንተን በዚህም ላይ ተመስርቶ ውሳኔዎችን የማሳለፍ አቅም ያላቸዉ፣ ፈጠራን እና አዲስ አስተሳሰብን የሚያበረታቱ፣ ሠራተኞቻቸውን ለማትጋት የቻሉትን ርቀት የሚጓዙ፣ የሚታዩ ኢ-ሥነምግባራዊ ድርጊቶችን በወቅቱና በቦታው የማስተካከል ብቃትና ክህሎትን የተላበሱ ናቸዉ፡፡ ሥነምግባር የተላበሱ መሪዎች ሁሌም ቢሆን የግል ባህሪያቸውን እና እሴቶቻቸውን ለመፈተሽ እና ለማስተካከል ቁርጠኛና ትጋት አላቸዉ፡፡ በተጨማሪም ለህግ ተገዥ የሆኑና የሚወሰዷቸውን እርምጃዎችና ውሳኔዎች ውጤት ቀድመው መተንበይ የሚቻሉ እና ምንም ይሁን ምን ለውሳኔያቸው ኃላፊነትን የሚወስዱ በንግግራቸው ብቻ ሳይሆን በድርጊታቸው ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉ ናቸዉ፡፡ በአጠቃላይ መልካም ሥነምግባርን የተላበሱ መሪዎች ለመሆን ከላይ የተገለፁትን ባህሪያት ከማስመሰል ርቆ ከራስ ጋር ማዋሃድንና መተግበርን ይጠይቃል፡፡

በአንፃሩ የሰዎች የተደበቀ ወይም ግልጽ የሆነ ኢ-ሥነምግባራዊ ድርጊቶች የሚታዩት ሙሉ በሙሉ ከሰዎች እይታ እርቂያለሁ ወይም ተሰውሬያለሁ ብለው በሚያስቡበት ወቅት እንደመሆኑና ይህ ስብእና ደግሞ ዘላለማዊ ሳይሆን እንደሁኔታው ሊቀየርና ሊለምድ የሚችል በመሆኑ በእውነታው ዓለምም ጭምር ከሚፈጠሩ ክፍተቶችና ክስተቶች አንፃር እራስን እየመዘኑና እያበለፀጉ ቀጣይነት ባለው የዳበረ መልካም ሥነምግባር የመጓዝ ቁርጠኝነትን ይጠይቃል፡፡

በመሆኑም መሪዎች የቆሙበትን ሁኔታ ለመመዘንና ችግሮችን ከወዲሁ ለመከላከል "ልብ ያለዉ ልብ ይበል እንዲሉ" ሁሌም ቢሆን ወደራሳቸው ለማየት የሚረዳቸውን የሚከተሉትን መሰል የራስ መመዘኛ ጥያቄዎችን አያነሱ ውስጣቸውን መመዘን ሊኖርባቸው ይገባል፡፡

- ቀኑን ሙሉ ያከናወንኳቸው ተግባራት በዙሪያዬ ያሉ የቅርብ ሰዎች ቢያውቋቸው ምን ሊሰማቸው ይችላል?
- በኃላፊነት ዘመኔ ምን ትርጉም ያለው ሥራ መስራት እፈልጋለሁ የእስካሁን አካሄዴስ ይህን ያመላክታል?
- እኔ ከተቋሜ ስለቅ በነበረኝ ቆይታ ቀሪ የተቋሙ አባላት በምን መልክ እንዲያስታውሱኝ እፈልጋለሁ?
- በሰራሁባቸው ተቋቋማትና በህይወት ከነበርኩበት ኃላፊነት ስለቅ ለቤተሰቦቼ የምተርክላቸው እኩሪ ነገር አለኝ?
- ልጆቼ ወይም የቅርብ ሰዎች ቢያውቁ ምን ያህል ይኮሩብኛል?
- ሁሉም ሰው የእኔ አይነት አስተሳሰብ እና ስብዕና ቢኖረው አካባቢያችን ወይም ዓለማችን ምን አይነት ገጽታ ይኖራታል?
- ያስቀመጥኳቸው እሴቶች በግል ተጎጅ ቢያደርጉኝ እንኳ ምን ያክል በጽናት ይዣቸው እዘለቃለሁ?
- ለምመራው ተቋምና ማህበረሰብ ምን አይነት እሴቶች እና አመለካከቶች ቢቀየሱና ቢተገበሩ ሊጠቅሙ ይችላሉ?
- የትኞቹን መሪዎችና ባህሪያቸውን አደንቃለሁ እኔስ ከእነሱ አንጻር ምን ይጎድለኛል?
- ዋነኞቹ እሴቶቼና መርሆዎቼ ምንድን ናቸው፤ ድርጊቴስ ይህን የሚያረጋግጥ ነው?
- በዙሪያዬ ያሉ የስራ አጋሮቼና ወዳጆቼ በመርሆዎቼ እና እሴቶቼ ዙሪያ ባለኝ ጥንካሬ እንዴት ይመዝኑኛል?
- በተቋሜ ውስጥ ያለኝን ቦታ ወይም ኃላፊነት ለመልቀቅ እንድወስን ሊያስገድዱኝ/ ሊያደርጉኝ የሚችሉ ስህተቶች ወይም ኢ-ሥነምግባራዊ ድርጊቶች ምንድን ናቸው?

የሚሉና መሰል አንቂ ጥያቄዎችን ወደራስ በማምጣትና የህሊና ፍርድ በመስጠት ነቅቶ መጓዝን በሚታዩ ጉድለቶች ላይም ፈጣን ማስተካከያዎችን እያስቀመጡ መሄድን የሚጠይቅ ይሆናል፡፡

ከላይ የተገለፁት እውነታዎች ጥሩ አካባቢ፣ በኢኮኖሚ የበለፀገች ሀገርና ዓለምን ለመገንባት ያላቸው ጠቀሜታ ጥያቄ ውስጥ የሚገባ ባይሆንም ተፈፃሚነታቸው የመናገርን ያክል ቀላልና አልጋ በአልጋ ሆነው የሚታዩ አይሆንም፤ ይልቁንም በበርካታ ውስጣዊና ውጫዊ መሰናክሎች የተሞሉ እንጂ፡፡

በመሆኑም መሪዎች በሥነምግባራዊ አመራር ውስጥ ሊገጥሟቸው የሚችሉ ፈታኝ ሁኔታዎችን ማየትና ለእነዚህ መሰናክሎች ከወዲሁ መፍትሄ እያስቀመጡ መሄድን እንደ ቁልፍ ተግባር ሊወስዱት ይገባል፡፡ ከእነዚህ አስቸጋሪ ወይም ፈታኝ ሁኔታዎች ተብለዉ ከሚጠቀሱት ጉዳዮች መካከል ውሳኔ ለመስጠት ፈታኝ(አስገዳጅ) ነባራዊ ሁኔታዎች ማጋጠም፣ የከባቢያዊ ሁኔታዎች ወይም የተቋማት የቆየ ባህል በውሳኔ አሰጣጥ ላይ የሚፈጥረው የነፃነት ችግር፣ ለውሳኔ አሰጣጥ የማያመቹ ግራጫ አካባቢዎች (Gray Areas) መኖር፣ ፈጣን የሆነ የማህበረሰቡ ፍላጉት እድገትና ለውጥ፣ ፈጣን የሆነ የአመለካከለት ለውጥና ሥለመሪዎቹ ያለው እይታና ክትትል መጨመር፣ የሥራ ዘርፉ በአዲሱ ወጣት ትውልድ መተካትና ይህም ኃይል ሥራ እና ውጤትን በሚመለከት ለረዥም ጊዜ ከተለመደው የተለየ ምልከታ ይዞ መምጣት፤ በተለይም በማንኛውም መልኩ ውጤትን ማምጣት ማለትም የመጨረሻው ውጤት እስካማረ ድረስ ውጤቱ የተገኘበት መንገድ አያስጨንቅም (The end justifies the means) አመለካከትን ይዞ የሚጓዝ መሆኑ ከብዙ በጥቂቱ የሚጠቀሱ ናቸዉ፡፡

እነዚህና መሰል ሁኔታዎች በአመራሩ ላይ ሥነምግባራዊ አመራር ለመስጠት በሚያደርገው ጥረት በአንድ በኩል ጥረቶች በተጓደሉ ቁጥር እንደ እንቅፋት በሌላ በኩል ደግሞ ጥረቶችና ጥንካሬዎች በጨመሩ ጊዜ ደግሞ እንደ ምቹ ሁኔታ /አንቂ ሁኔታ/ የሚታዩ ናቸው፡፡

አገራችን ኢትዮጵያ ከአፍሪካ ቀዳሚ የብልጽግና ተምሳሌት የመሆን ራዕይን ሰንቃ እንቅስቃሴ ጀምራለች፡፡ በመንግስት የአስር ዓመት የልማት ዕቅድ ውስጥም በመንግስት ብቁ፣ ገለልተኛና ነጻ የሕዝብ አገልግሎት ስርአት በመገንባት የመንግስትን የመፈጸም ብቃት በማጎልበትና መልካም አስተዳደርን በማስፈን የዜጎችን እርካታ ማሳደግ አንዱ ዓላማ ሆኖ ተመላክቷል፡፡ ለዚህ አገራዊ ራዕይ እውን መሆንና ለዓላማው መሳካት መልካም ሥነምግባርን በማስፈንና ሙስናና ብልሹ አሰራርን በመከላከል ሌብነትን የሚጸየፍ፣ ምርታማና ታታሪ ትውልድ መፍጠር ትኩረት የሚሰጠው መሆን ይገባዋል፡፡

ለዚህ ስኬት እውን መሆን ደግሞ በዋነኝነት በሥነምግባር የታነጸ ቁርጠኛና ምርታማ አመራር ሊኖር ይገባል፡፡ ከዚህ አንጻር እስካሁን የሄድንበት ሂደት ቆም ብለን እራሳችንን እንድንፈትሽ ያስገድዳል፡፡ በሥነምግባራቸው ምልኡ የሆኑና የበለጸጉ መሪዎች ሃገርን ብሎም ዓለምን ይሞላሉ ያበለጽጋሉ፤ በተቃራኒው የጎደሉና ያልበለጸጉ ከሆነ ሀገርን ብሎም ዓለማችንን ያጎድላሉ ያፈርሳሉ፡፡

በመሆኑም በሀገራችን የሚደረገውን የፀረ-ሙስና እንቅስቃሴ ከግብ ለማድረስ በላቀ የአመራር ሥነምግባር አርአያ ሆኖ በመገኘትና በመምራት የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት ለመወጣት ተገቢውን ጥረት ማድረግ የሥራ ድርሻ ብቻ ሳይሆን የዜግነትና ሰውነት ግዴታም ይሆናል፡፡

# የሥነምግባር አምባሳደሮች

በመንግስታዊ ተቋማትም ሆነ መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት ውስጥ በተለያዩ ዘርፎች የላቀ ውጤት ላስመዘገቡና ለሌሎች አርዓያ የሚሆን ተግባር ላከናወኑ ግለሰቦችና ድርጅቶች ሽልማትና እውቅና የመስጠት ልምድ በውጪ አለም ረዥም ጊዜን ያስቆጠረ ነው፡፡ በሀገራችንም በተለያዩ የሙያ መስኮች የላቀ ውጤት ላስመዘገቡና ለሌሎች ምሳሌ ለሆኑ ግለሰቦችና ተቋማት እውቅና፣ ሽልማትና ክብር መስጠት እየተለመደ መጥቷል፡፡

በላቀ ሥራቸውና በመልካም ሥነምግባራቸው ምሳሌ ለሚሆኑ አካላት የሚሰጠው ሽልማት ወይም እውቅና የገንዘብ፣ የቁሳቁስ፣ የምስጋና የምስክር ወረቀት ወይም በየተሰማሩበት ዘርፍ የአምባሳደርነት ስያሜ በመስጠት ሊሆን ይችላል፡፡ ዋና ዓላማው ግለሰቦቹን ወይም ተቋማቱን ለበለጠ ሥራ በማነሳሳት በየተሰማሩበት ዘርፍ ውጤታማ እንዲሆኑ ለማስቻልና ሌሎችም የእነሱን አርአያ እንዲከተሉ ለማድረግ ነው፡፡

በአለም ላይ ከሚከናወኑ የሽልማትና የእውቅና ፕሮግራሞች መካከል በስፖርት፣ በሙዚቃና በኪነጥበብ ሥራዎች ላይ የሚያተኩሩት ሰፊ ሽፋን ያላቸውና ጎላ ያሉ ቢሆንም በየተሰማሩበት የሙያ መስክ በሚያሳዩት መልካም ሥነምግባርና ሙስናና ብልሹ አሠራርን በመከላከል ከፍተኛ አስተዋፅኦ ላበረከቱ አካላት የሚሰጥ እውቅናና ሽልማትም ይከናወናል፡፡ የዚህ አይነቱ የእውቅናና የሽልማት ፕሮግራም ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል እንደ አንድ የሙስና መከላከያ ዘዴ ይወሰዳል፡፡

በዚህ ረገድ እንደምሳሌ የሚጠቀሱ የመልካም ሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና የሽልማትና የእውቅና መድረኮች አሉ፡፡ መንግስታዊ ካልሆኑና ለትርፍ ካልተቋቋሙት ድርጅቶች መካከል በአርሜናዊቷ የፀረ-ሙስና ታጋይ አማሊያ ኮስታንያን ስም የተሰየመው ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል አማሊያ ሽልማት (Transparency International Amalia Award) እንደ አብነት ሊጠቀሱ ይችላል፡፡ የአርሜንያ ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል ቻፕተር ሀላፊዋ አማሊያ በፀረ-ሙስና ትግል ውስጥ የነበራት አስተዋፅኦ እጅግ ከፍተኛ እንደነበር ይጠቀሳል፡፡ በፀረ-ሙስና ትግል በግንባር ቀደምትነት የምትጠቀሰዋ ይህች ጠንካራ እንስት በሥራዋ ላይ እንዳለች በድንገት ህይወቷ ያለፈው እ.አ.አ በ2010 ነበር፡፡ እሷን ለማስታወስ ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል አማሊያ ሽልማት በሚል ርዕስ በፀረ-ሙስና ትግል ዙሪያ የላቀ ተግባር ላከናወኑ ግለሰቦች በየዓመቱ እውቅናና ሽልማት ይሰጣል፡፡

ሌላው እንደአብነት ሊጠቀስ የሚችለው በአሜሪካ የሥነምግባር ጥምረት ሽልማት (Coalition for Integrity's Integrity Award, USA) ነው፡፡ ይህ ተቋም በዋነኝነት እውቅና የሚሰጠው ሙስናን ለመከላከል የሚያስችል ዘመናዊ የአሠራር ዘዴ በአሜሪካና ከአሜሪካ ውጭ በሚገኙ የመንግስት፣ የግልና የሲቪክ ማህበራት ውስጥ ለሚሠሩ ግለሰቦችና ድርጅቶች ነው፡፡ ይህን የላቀ ሥነምግባር ሽልማት (Integrity Award) ካገኙ ታዋቂ ሰዎች መካከል የአሜሪካው ሴናተር ጆን ማኬን፣ የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዝደንት ጂሚ ካርተር፣ የቀድሞው የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሂላሪ ሮድሀም ክሊንተን፣ የቀድሞው የአለም ባንክ ግሩፕ ፕሬዝደንት ሰር ጀምስ ዎልፍንሰን እና ሌሎችም ይጠቀሳሉ፡፡

መንግስታዊ ከሆኑት ውስጥ ደግሞ የኬንያን የሲቪል ሰርቪስ የልህቀት ሽልማትን (Public Service Excellence Award, Kenya) ማንሳት ይቻላል፡፡ የኬንያ ሲቪል ሰርቪስ የልህቀት ሽልማት ይህን ሽልማት የሚያዘጋጀው በዋናነት የመንግስት የሥራ ሀላፊዎች በመንግስት ተቋማት የሚታየውን የአገልግሎት አሰጣጥ ችግር እንዲያሻሽሉ ለማነሳሳትና ለማገዝ ነው፡፡ ይህ ሽልማት ፕሮግራም የተጀመረው እ.አ.አ በ2015 ሲሆን በሲቪል ሰርቪስ ውስጥ የላቀ ውጤት ላስመዘገቡና በሥነምግባራቸው ለተመሰገኑ የሲቪል ሰርቪስ ሰራተኞች ነው፡፡ ይህ ስራ በአንድ ወቅት በሀገራችንም ተጀምሮ የነበረ ነው፡፡

ሌላው Integrity Idol በመባል የሚታወቀው አለም አቀፍ ንቅናቄ ነው፡፡ ኢንተግሪቲ አይዶል በዋናነት እውቅና የሚሰጠው ታማኝና መልካም ሥነምግባር ላላቸው የመንግስት ባለሥልጣናት ነው፡፡ ይህም ባለሥልጣናቱ ይበልጥ ታማኝ እንዲሆኑና ሌሎችም የእነሱን መልካምነት እንዲከተሉ ለማድረግ ነው፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን መልካም ሥነምግባርን ለማበረታታትና ሙስናን ለመከላከል የሚሰጡ የሽልማትና የእውቅና ዝግጅቶችን ለአብነት ጠቃቀስን እንጂ ሌሎች በርካታ ተመሳሳይ ዝግጅቶች በየሀገሩ፣ በየአህጉሩና በአለም አቀፍ ደረጃ ይካሄዳሉ፡፡

እነዚህን ተሞክሮዎች ያነሳነው በሀገራችን በተለይ የመልካም ሥነምግባር ተግባራትን ለማበረታታትና ሙስናን ለመከላከል እንደ አንድ የሙስና መከላከያ ዘዴ ጥቅም ላይ የሚውለውን በዘርፉ የላቀ አስተዋፅዖ ላበረከቱ ግለሰቦችና ድርጅቶች ሽልማትና እውቅና የመስጠት ጅማሮን ለመቃኘት ነው፡፡

በሀገራችን በተለያዩ ዘርፎች የላቀ አስተዋፅኦ ያበረከቱ ግለሰቦችና ተቋማትን ለማበረታታት የሚሰጡ የዕውቅና ፕሮግራሞች የሚያበረታቱና በመጠንም በጥራትም ተጠናክረው መቀጠል ያለባቸው ናቸው፡፡ በዚህ ፅሁፍ የሚዳሰሰው ግን በሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ዙሪያ ያሉ ጅምር ተግባራትን ይሆናል፡፡

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በሥነምግባር ግንባታና በፀረ-ሙስና ትግል እንቅስቃሴ ሂደት ግንባር ቀደም ሚና የነበራቸዉን እና ላቅ ያለ አስተዋጽኦ ያላቸዉን ግለሰቦችና ተቋማት መሸለምና እዉቅና መስጠት ለፀረ-ሙስና ትግሉ የሚያበረክተውን አስተዋፅኦ በመረዳት እንቅስቃሴ ማድረግ ጀምሯል፡፡

በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1236 አንቀፅ 7 ቁጥር 8 መሠረት ሙስናን በመከላከልና በመታገል ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ላበረከቱ አካላት እውቅናና ሽልማት እንዲያገኙ ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ እንደሚያደርግ በግልፅ በተደነገገው መሠረት ኮሚሽኑ ይህን ተግባራዊ ለማድረግ በቅርቡ የአፈፃፀም መመሪያ አውጥቷል፡፡ የዚህ መመሪያ ዋና ዓላማው፡-

- ሙስናን በመታገል እና በመከላከል ረገድ ጥሩ ዉጤት ያስገኙ ሰዎች፣ መሥሪያ ቤቶች እና የልማት ድርጅቶች ላበረከቱት

## መልካም ዜና




አስተዋጽኦ ተገቢዉን ዕውቅና፣ ሽልማትና ምስጋና ለመስጠት፣

- በፀረ-ሙስና ትግሉ የሌሎችን ተነሳሽነት እንዲጨምር በማድረግ መልካም ሥነምግባር በሀገሪቱ እንዲስፋፋና እንዲጎለብት ለማድረግና
- በፀረ-ሙስና ትግሉ ስራዎችን በመተግበር ሂደት የተገኙ መልካም ተሞክሮዎችንና ልምዶችን በመቀመር ለሌሎች ግለሰቦችና ተቋማት ተደራሽ ማድረግ ነው፡፡

የአፈፃፀም መመሪያው የእውቅናና የሽልማት ሥርዓቱ ተአማኒነት ባላቸዉና ተጨባጭ በሆኑ መረጃዎች ላይ የተመሰረተ፣ ግልፅነት ያለዉ እና ከአድልኦ የፀዳ፣ አሳታፊና ሚዛናዊ አሠራርን የተከተለ፣ የሴቶችና ወጣቶች ተሳትፎን ያረጋገጠ እንዲሆን የሚያስችሉ መርሆዎችንም ያካተተ ነው፡፡

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በ2012 ዓ.ም አለም አቀፍ የፀረ-ሙስና ቀንን ባከበረበት ዝግጅት ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ በሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ዙሪያ የላቀ አስተዋፅኦ ላበረከቱ ግለሰቦችና ድርጅቶች የእውቅና ፕሮግራም አዘጋጅቶ ነበር፡፡ በዚህ የሽልማት ፕሮግራም ላይ ሥነምግባርን በማጎልበትና የፀረ-ሙስና ትግል እስከ ህይወት መስዋዕትነት ለከፈሉ 9 ግለሰቦች እውቅና ሰጥቷል፡፡

በ2013 ዓ.ም የኮሚሽኑን 20ኛ ዓመት የምስረታ በዓል ምክንያት በማድረግ ኮሚሽኑ ለሁለተኛ ጊዜ በሥነምግባር ግንባታና በፀረ-ሙስና እንቅስቃሴ ሂደት ግንባር ቀደም ሚና ለነበራቸዉ እና ላቅ ያለ አስተዋጽኦ ላበረከቱ ተቋማትና ግለሰቦች እዉቅናና ሽልማት የመስጠት ተግባር ተከናውኗል፡፡

በዚህ የእውቅናና የሽልማት ፕሮግራም ላይ በርከት ያሉ አካላት እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡

እንደሚታወቀው የፀረ-ሙስና ትግል በዋናነት የህብረተሰቡን ተሳትፎና ድጋፍ የሚጠይቅ ነው፡፡ የችግሩ ገፈት ቀማሽ የሆነዉ መላዉ ህብረተሰብ የችግሩ መሻገሪያ መንገድን ለማበጀትም ሚናዉ የጎላ ነዉ፡፡ ሙስናን መዋጋት ከራስ ይጀምራል እንዲሉ የእያንዳንዱ ግለሰብ የተናጠል እንቅስቃሴ የችግሩን ማህበረሰባዊና ሀገራዊ ይዘት በእጅጉ ይወስናል፡፡ ይህ ደግሞ ከሚገለጽባቸዉ ጉዳዮች መካከል

- ባለን ማህበራዊ መስተጋብር የመልካም ሥነምግባር አርአያ ሆኖ በመገኘትና በድርጊታችን አካባቢያችን ላይ በምንፈጥረዉ ተጽእኖ፣
- ማህበረሰቡን በማንቃትና በማስተማር በምናደርገዉ አስተዋጽኦ፣
- በተሠማራንበት የሥራ ዘርፍ የሙያ ሥነምግባራችን የሚጠይቀዉን ሙያዊ ብቃትና ስብእና አሟልተን በመንቀሳቀስ፣
- የሙስና ወንጀሎችን አይቶና ሰምቶ ከማለፍ ይልቅ በያገባኛል ባይነት በማጋለጥ/በመጠቆምና አስፈላጊዉን ምስክርነት በመስጠት/...ወዘተ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ተጠቃሾች ናቸዉ፡፡

በዚህ ረገድ ጥቂት የማይባሉ ግለሰቦች ከፍተኛ የሆነ አስተዋፅኦ ሲያበረክቱ ቆይተዋል፡፡ በመሆኑም በዚሁ መሠረት ከተለያዩ ዘርፎች ለተመረጡ ግለሰቦች እውቅናና ሽልማት ተሰጥቷል፡፡ ከነዚህ መካከል መምህራን፣ የጤና ባለሙያዎች፣ የፍት አካላት፣ የመገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች፣ በተቋማት የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና አስፈፃሚዎች፣ የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ተቋማት ሠራተኞች እንዲሁም በሥነምግባራቸው ሞዴል የሆኑ ግለሰቦችና ተቋማት ይጠቀሳሉ፡፡

ትምህርት የሀገር ሁለንተናዊ ልማት መሰረት ነዉ፡፡ በዚህ ዉስጥ ደግሞ ዋና ተዋናይ የሆኑት መምህራን ከሙያዊ ብቃት ባሻገር ያላቸዉ የሥነምግባር ደረጃ ቁልፍ ሚና እንዳለዉ ይታመናል፡፡ ከዚህም በመነሳት

- ለተማሪዎቻቸዉና የሙያ አጋሮቻቸዉ በበጎ ምግባር አርአያ መሆን የቻሉ፣
- የታታሪነት ተምሳሌትና ለሀገር የሚጠቅሙ የምርምር ስራዎችን ያበረከቱ፣
- ራስን ለማብቃትና ሙያዊ ብቃትን ለማሳደግ የጣሩ፣
- ለሥነምግባር ደንብና ሥራ ዲሲፕሊን ፍጹም ተገዥ የሆኑ፣
- ሙስና እና ኢ-ሥነምግባራዊ ድርጊቶችን የተፀየፉና የታገሉ

በየተቋማቸው ለተለዩ 15 የዩኒቨርሲቲ መምህራን፣ ከ10 ክልሎች ለቀረቡ 30 መምህራን፣ 7 ከሁለት ከተማ አስተዳደሮች ለተለዩ መምህራን በድምሩ ለ52 መምህራን እውቅናና ሽልማት ተሰጥቷል፡፡

የጤናዉ ዘርፍ ለማህበረሰቡ ወሳኝ የሆነ አገልግሎት የሚሰጥ ዘርፍ ሲሆን ለስኬታማነቱም በተለያየ ደረጃ የሚገኙ ባለሙያዎችን በሥነምግባር የታነጸ እንቅስቃሴና ተሳትፎ በእጅጉ ይጠይቃል፡፡ በዚህም መሰረት፡-

- በተቋማት ዉስጥም ሆነ በተገልጋዮች ዘንድ በመጥፎ ሥነምግባር የማይነሱ ይልቁንም በበጎ ምግባራቸዉ ተጠቃሽ የሆኑ፣
- ሙያዊ ሥነምግባራቸዉን ጠንቅቀዉ የሚረዱ-ሙያቸዉን አክባሪና አስከባሪ፣
- ተገልጋዮችን በሰብአዊ ክብር እና በእኩልነት የማስተናገድ ባህሪ የተላበሱ፣
- ታታሪ ፣ራሳቸዉን ለማብቃትና ሙያዊ አቅማቸዉን ለማሳደግ ሁሌም የሚተጉ፣
- ለተቋማት የሥነምግባር ደንብና ሥራ ዲሲፕሊን ፍጹም ተገዥ የሆኑ፣
- ሙስና እና ኢ-ሥነምግባራዊ ድርጊቶችን የሚጸየፉና የሚታገሉ፣

መሆናቸዉ በተቋማቱ ተጣርቶና ተረጋግጦ ለቀረቡ 5 የፌዴራል ሆስፒታሎች፣ ለ30 ክልል አስተዳደር ጤና ተቋማትና ለ3 የከተማ አስተዳደር ጤና ባለሙያዎች በድምሩ ለ38 የጤና ባለሙያዎች እውቅናና ሽልማት ተሰጥቷል፡፡

በሙያዊ ሥነምግባር የታነጸ የፍትህ ዘርፉ የዜጎችን የፍትህ ጥያቄ በአግባቡ ለማስተናገድ ከሚኖረዉ ድርሻ ባሻገር በአጠቃላይ በፀረ-ሙስና ትግሉ ዉጤታማነት ላይ ያለዉ ወሳኝነት የጎላ ነዉ፡፡ በሙስና የተተበተበ የፍትህ ስርአት ባለበት ሀገር የፀረ-ሙስና ትግል ብሎ ነገር ከቃላት የዘለለ ትርጉም አይኖረውም፡፡ በዚህ መሠረት፡-

- ለዜጎች የፍትህ ጥያቄ መረጋገጥ ሙያዉ የሚጠይቀዉን ስነምግባር ተላብሰዉ ድርሻቸዉን የሚወጡ
- በመጥፎ ስነምግባር የማይነሱ ይልቁንም በበጎ ምግባራቸዉ ለሙያ አጋሮቻቸዉ አርአያ የሆኑ፣
- ለተቋማት የሥነምግባር ደንብና ሥራ ዲሲፕሊን ፍጹም ተገዥ የሆኑ፣
- ሙስና እና ኢ-ሥነምግባራዊ ድርጊቶችን የሚጸየፉና የሚታገሉ፣

መሆናቸዉ በፌዴራል፣ በክልልና በሁለቱ የከተማ አስተዳደር የፖሊስ ኮሚሽኖች ተለይተዉ ለቀረቡ 44 የፖሊስ አባላት፣ በፌዴራልና በክልል ጠቅላይ አቃቤ ህግና የአቃቢያን ህግ አስተዳደር ጉባኤ ለተለዩ ከፌዴራል ጠቅላይ አቃቤ ህግ ለ9 ከክልል 27 አቃቢያን ህግ ፣ በዳኝነት ሥርአቱ ዉስጥ በፍርድቤቶችና በዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ምዘና መሠረት ለ24 ዳኞች እውቅናና ሽልማት ተሰጥቷል፡፡

የጋዜጠኝነት ሙያ ከሚጠይቀዉ ሙያዊ ሥነምግባር ባሻገር በተለይም በምርመራ ጋዜጠኝነትና፣ ሥነምግባር ግንባታ እንዲሁም

ሰፊ የሆነ ማህበራዊ ንቅናቄን በመፍጠር ረገድ በትግሉ ዉስጥ ጉልህ የሆነ ድርሻ እንዳለዉ ይታመናል። ከዚህ አንጻር በሙያ ሥነምግባር የታነጸ ስብእና እንደቀዳሚ የዉጤታማነት ቅድመ ሁኔታ ይታያል። በዚህም መሠረት፡-

- በሥነምግባር ግንባታ እና ሙስና መከላከል ስራዎች ላይ ጉልህ አስተዋጽኦ ያላቸዉ፣
- የተዛባ መረጃን ከማሰራጨት የተጠበቁ፣ በሚዛናዊነት፣ በእዉቀትና በእዉነት ላይ ለመመስረት የሚታትሩና ሙያዊ ሀላፊነታቸዉን የሚወጡ፣
- ራስን ለማብቃትና ሙያዊ ብቃትን ለማሳደግ ሁሌም የሚተጉ፣
- ሙያዊ ሥነምግባርን ጠብቆ ሀላፊነት በመወጣት ለሌሎች አርአያ መሆን የሚችሉ፣
- በተሰማሩበት ሥራ ባላቸዉ የሥራ ትጋትና የሥራ ዲሲፕሊን በተቋሙ ዉስጥ ብቻ ሳይሆን በማህ/ሰቡ ዘንድ የተሻለ ተቀባይነት ያተረፉ፣

መሆናቸዉ በተቋማት ተለይተዉ ለቀረቡ፣ በተገልጋዮች አስተያየትና ጥቆማ ለቀረቡና ለተመረጡ፣ በምዘና ሂደቱም የተሻለ ዉጤት ላገኙ 5 ጋዜጠኞች እውቅናና ሽልማት ተሰጥቷል።

የሥነምግባር ግንባታና ሀገር አቀፍ የሙስና መከላከል ሥራን በባለቤትነትና በሀላፊነት መንፈስ እንዲተገብሩት ለማድረግ በሚካሄደዉ ጥረት በፌደራልና በክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች እና በተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች ውስጥ የሚሠሩ ባለሙያዎች ቁልፍ ድርሻ እንዳላቸዉ ይታመናል። ከዚህም በመነሳት በፀረ-ሙስና ተቋማት ውስጥ እና በመንግስት ተቋማት ዉስጥ የሚሰሩ የሥነምግባር መከታተያ ሥራ አስፈፃሚዎች በሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ሥራ ላይ በነበራቸዉ ጥረትና ባስመዘገቡት ዉጤት መሠረት ለ15 የፌዴራልና የክልል የፀረ-ሙስና ተቋማት ሠራተኞች፣ ለ31 የፌደራል መንግስት ተቋማት፣ ለ16 የከተማ አስተዳደሮች፣ ለ20 የክልል አስተዳደሮች በድምሩ በድምሩ ለ82 የፀረ-ሙስና ተቋማትና የሥነምግባር መከታተያ ክፍል አስፈፃሚዎች እውቅናና ሽልማት ተበርክቷል።

ማህበረሰቡ በሥነምግባራቸዉ አርአያ የሆኑና በፀረ-ሙስና ትግሉ የተለየ አስተዋጽኦ ያላቸዉን ግለሰቦች ሙስናና ኢ-ሥነምግባራዊ ድርጊትን የሚጸየፉና የሚታገሉ፣ በሥነምግባር ግንባታ በተጨባጭ ሊታይ የሚችል ሥራ ያከናወኑ፣ በሙስና መከላከል ሥራ በተጨባጭ ሊታይ የሚችል ሥራ ያከናወኑ፣ በአርአያነት የሚቀርብ የመልካም ሥነምግባር መገለጫ ያላቸዉ በመሆናቸዉ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከማህበረሰቡ የቀረቡ ጥቆማዎችን መሰረት በማድረግና ተገቢዉን የማጣራትና የምዘና ሥራ በማከናወን ለ5 ግለሰቦች እውቅናና ሽልማት ተሰጥቷል።

ግለሰቦች በፀረ-ሙስና ትግል ውስጥ ያላቸውን ድርሻ ያህል ተቋማትም ከፍተኛ ድርሻ አለባቸው። ከዚህ አንፃር ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የሚያስችሉ ስርአት/አሰራሮችን በመዘርጋት፣ አደረጃጀቶችን በመፍጠር፤ የሥነምግባር ግንባታ ስራዎችን በሰፊው በመስራት፤ ለሙስና ብልሹ አሰራር ቀዳዳ የሚከፍቱ አሰራሮችን ለመድፈን የሚያስችሉ ጥናቶችን በማጥናትና በመተግበር፤ የሀብት ምዝገባ ስርአትን በመዘርጋት ቀዳሚና ከፍተኛ አፈፃፀም በማሳየት የተለዩ 10 የሲቪክ ማህበራት፣ የፌደራልና የክልል የመንግስት ተቋማት እውቅናና ሽልማት ተሰጥቷቸዋል።

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል የላቀ አስተዋፅኦ ላደረጉ ግለሰቦችና ተቋማት እውቅናና ሽልማት መስጠት በፀረ-ሙስና ትግሉ ውስጥ ያለውን ድርሻ በአግባቡ ይገነዘባል። ሙስናን የመከላከል ተግባር በአንድ ወይም በተወሰኑ አካላት ጥረት ብቻ ውጤታማ መሆን አይችልም። ስለሆነም የፀረ-ሙስና ትግሉ ሰፊ መሠረት እንዲኖረው ማድረግ ያስፈልጋል። ለዚህ ደግሞ ሙስናንና ብልሹ አሠራርን በመከላከል ሥራ የላቀ ተግባር ላከናወኑና ለሌሎች አርአያ መሆን ለሚችሉ ግለሰቦችና ተቋማት ክብር ሲኖረንና ለሥራቸውም መልካም እውቅና መስጠት ስንችል ነው።

ከዚህ አንፃር ኮሚሽኑ ተጨባጭ፣ አሳታፊና ውጤታማ የሆነ ጠንካራ የእውቅናና የሽልማት ሥርዓት በመገንባት ካለፉት ጊዜያት በተሻለ መንገድ ለማከናወን የሚያስችል ግልፅ የአሠራር መመሪያ የተዘጋጀ ሲሆን ተግባሩ ሳይቆራረጥ እንዲከናወንም በኮሚሽኑ ስትራቴጂክ እቅድ ጭምር የተካተተ ነው። ይህ ስራ የሥነምግባር አምባሳደሮችን የመፍጠርና የማብዛት ሥራ ነው። ለዚህ ስራ ውጤታማነት የሁሉም ተሳትፎና ትብብር አስፈላጊ በመሆኑ ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ ይገባል።